# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ማክሰኞ | 82ኛ ዓመት ቁጥር 024 መስከረም 24 ቀን 2015 ዓ.ም ዋጋ 10.00 | ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!



ደርባ ሚድሮክ ሲሚንቶ ኃ/የተ/የግል ማህበር



በልዩ የደርባ ሲሚንቶ መስመር 8688 ወይም
– 0111 26 26 27 – 0922 11 53 24/26
– 0111 26 26 28 – 0922 72 74 48/49
– 0111 26 26 29 – 0922 72 38 70
– 0111 26 26 30 – 0922 72 38 72
ፋክስ፡- 0111 26 23 45 እና
0111 26 23 18
ይዘዙን
ደረጃቸውን ጠብቀን የምናመርታቸውን ጥራት ያላቸው የሲሚንቶ ምርቶች ቤትዎ ወይም ፕሮጀክትዎ ደጃፍ ላይ ያለውጣ ውረድ በደርባ ትራንስፖርት ኃ.የተ.የግ.ማ አማካይነት እናቀርባለን።
ነገን ዛሬ እንሥራ







**ከ976 ሺህ በላይ ተማሪዎች በመጀመሪያው ዙር ይፈተናሉ**

## የአፈታተን ሥርዓቱ ተማሪዎችን ከፈተና ስርቆትና ኩረጃ በመጠበቅ ተረጋግተው እንዲፈተኑ ያስችላል



ፕሮፌሰር ብርሃኑ ነጋ

**ዘላለም ግዛው**

አዲስ አበባ፡- የ2014 ዓ.ም የ12ኛ ክፍል መልቀቂያ ብሔራዊ ፈተና የአፈታተን ሥርዓቱ ተማሪዎችን ከፈተና ስርቆት፣ ከኩረጃ እና ከሐሰተኛ መልስ ስርጭት በመከላከል ተረጋግተውና የራሳቸውን አቅም ተጠቅመው እንዲፈተኑ እንደሚያስችል የትምህርት ሚኒስትሩ ፕሮፌሰር ብርሃኑ ነጋ ገለጹ፡፡

የ2014 ዓ.ም የ12ኛ ክፍል መልቀቂያ ብሔራዊ ፈተና አስመልክቶ ትናንት የትምህርት ሚኒስትሩ ፕሮፌሰር ብርሃኑ ነጋ፣ ሚኒስትር ዴኤታው ዶክተር ፋንታ ማንደፍሮ እና የአገር አቀፍ ትምህርት ምዘናና ፈተናዎች አገልግሎት ዋና ዳይሬክተር ዶክተር እሸቱ ከበደ በጋራ መግለጫ ሰጥተዋል፡፡

የ2014 ዓ.ም የ12ኛ ክፍል መልቀቂያ ብሔራዊ ፈተና የመጀመሪያ ዙር ተፈታኞች 976 ሺህ 18 መሆናቸውን እና ከጸጥታ ጋር ተያይዞ 56 ሺ. ተፈታኞች በመጀመሪያው ዙር እንደማይፈተኑ ኃላፊዎቹ ገልጸዋል፡፡

የአፈታተን ሥርዓቱ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል



## “መንግሥት ረሃብን እንደ ጦር መሣሪያ ተጠቅሟል የሚለው የኮሚሽኑ ‹ሪፖርት› የፖለቲካ ሸፍጥ ነው”

-ኮማንደር ገ/መስቀል ወልደሚካኤል

**መኣርግ ገ/ሔር**

አዲስ አበባ፡- ሰብአዊ ረድኤት ወደ ትግራይ እንዳይገባ ጦርነት በመክፈት ሲያደናቅፍ የነበረው አሸባሪ የሕወሓት ቡድን ሆኖ እያለ የተባበሩት መንግሥታት የሰብአዊ መብት ባለሙያዎች ኮሚሽን ግን የፌዴራል መንግሥት ረሃብን እንደ የጦር መሣሪያ ተጠቅሟል የሚል «ሪፖርት» ማውጣቱ ሆን ብሎ የሚሠራ የፖለቲካ ሸፍጥ ነው ሲሉ የትግራይ ዴሞክራሲያዊ ፓርቲ (ትዴፓ) አባል ኮማንደር ገ/መስቀል ወልደሚካኤል ተናገሩ።

«መንግሥት ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል

## ሚኒስቴሩና ተጠሪ ተቋማቱ ለመከላከያ ሠራዊት ከ16 ሚሊዮን ብር በላይ ድጋፍ አደረጉ

**ሳሙኤል ወንደሰን**



አዲስ አበባ፡- የኢንዱስትሪ ሚኒስቴርና ተጠሪ ተቋማቱ ለመከላከያ ሠራዊት ከ16 ሚሊዮን ብር በላይ የሚገመት የገንዘብና የዓይነት ድጋፍ አደረጉ።

ድጋፉን ያስረከቡት የኢንዱስትሪ ሚኒስትሩ አቶ መላኩ አለበል ተቋማቱ ባለፈው ወር ለመከላከያ ሠራዊት 454 ዩኒት ደም ድጋፍ ማድረጋቸውን አስታውሰው፣ በትናንትናው ዕለትም በድምሩ 16 ሚሊዮን የሚያወጡ የተለያዩ ድጋፎችን ለመከላከያ ሠራዊት ማበርከታቸውን ተናግረዋል፡፡

እንደ ሚኒስትሩ ገለጻ፣ ሠራዊቱ ሕይወቱና አካሉን የሚሰጥላትን ኢትዮጵያ ለማቆም ከተረፈን ሳይሆን ካለን ላይ መስጠት ይጠበቅብናል፡፡ በዚህም መሠረት ቀደም ሲል 454 ዩኒት ደም በሚኒስቴሩ መስሪያ ቤት ሠራተኞችና በተጠሪ ተቋማቱ አማካኝነት ግንባር እየተፋለመ ላለው የመከላከያ ሠራዊታችን ለግሰናል፡፡

ድጋፉ 14ነጥብ 5 ሚሊዮን ብር በገንዘብና 1ነጥብ5 ሚሊዮን ደግሞ በዓይነት የተደረገ ነው ያሉት ሚኒስትሩ፣ የመከላከያ ሠራዊት አገርን ለማቆየት በሚያደርገው እንቅስቃሴ መስሪያ ቤቱ ምንጊዜም ከጎኑ እንደሚሆን ተናግረዋል።

ለመከላከያ ሠራዊት ከድጋፍ ባለፈ ለሠራዊቱ የሚሆኑ አልባሳትን፣ የደንብ ልብስና ጫማ በማምረት እያቀረቡ እንደሆነ የተናገሩት አቶ መላኩ፣ በ2015 ለሠራዊቱ የሚያስፈልጉ ምርቶችን በጥራት ለማምረት እንደሚሠሩም ተናግረዋል።

ድጋፉን የተረከቡት የመከላከያ ሚኒስትር ዴኤታ ማርታ ሊዊጂ በበኩላቸው፤ የኢንዱስትሪ ሚኒስቴርና ተጠሪ ተቋማት ከአመራርና ሠራተኛ ጋር በመሆን ለጀግናው መከላከያ ሠራዊት ስንቅ የሚሆን የገንዘብ፣ የደም ልገሳና የዓይነት ድጋፍ ስላቀረቡልን በመከላከያ ሚኒስቴር ስም አመሰግናለሁ ብለዋል፡፡

ከኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ጋር የሠራዊቱን አልባሳት በአገር ውስጥ እንዲመረት አብረን እየሠራን ነው ያሉት ወይዘሮ ማርታ፣ የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ከውጭ የሚገቡ ምርቶችን በአገር ውስጥ ለመተካትና ለሠራዊቱ በሚመጥን መልኩ ለማቅረብ ከፍተኛ ሥራ እየሠራ ነው ብለዋል።

ሚኒስቴሩና ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል



ጋዜጠኛ ሄኖክ ስዩም

## የአደባባይ በዓላት ተገቢውን ጠቀሜታ እንዲያስገኙ ባህላዊ እሴታቸውን ጠብቆ ማቆየት ያስፈልጋል

**ሳሙኤል ወንደሰን**

አዲስ አበባ፡- የአደባባይ በዓላት ተገቢውን ጠቀሜታ እንዲያስገኙ የሚገለጡባቸው ባህል፣ አለባበስና ጌጣጌጥ በዘመን አመጣሽ ፋሽን ተለውጠው የቱሪዝም ዘርፉን እንዳይጎዱ ከተለያዩ የባህልና የእሴት መበረዝ መጠበቅ ያስፈልጋል ሲል የቱሪዝምና የጉዞ ጋዜጠኛው ሄኖክ ስዩም ገለጸ።

ጋዜጠኛ ሄኖክ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደተናገረው፣ የኢትዮጵያ የአደባባይ በዓላት የሚገለጡበት የአከባበር ሥነ ሥርዓትና አለባበስ ከሌላው ዓለም የአደባባይ በዓላት የተለየ በመሆኑ በቱሪስቶች እንዲወደዱና እንዲጎበኙ ያደርጋቸዋል። ስለዚህ ይህ አከባበርና እሴት በዘመን አመጣሽ ድርጊቶች እንዳይበረዝ መጠበቅ ያስፈልጋል።

እንደ ጋዜጠኛው ገለጻ፣ በዓላት በአንድ ጊዜ የሚለወጡ ሳይሆን ከጊዜ ወደ ጊዜ በሚደረጉ አለባበስና ዘመን አመጣሽ ድርጊቶች የሚለወጡ በመሆኑ የማህበረሰቡን

የአደባባይ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል







ገጽ 3

ማረሚያ ቤቶች የታራሚዎችን ሰብአዊ ክብር የሚጠብቁና በሙያ አቅም የሚገነቡ መሆን አለባቸው

በኢፌዴሪ የመንግሥት ኮሙኒኬሽን አገልግሎት
FDRE Government Communication Service

# በዓላት በሠላማዊ ሁኔታ መከበራቸው የሕዝቡን የሠላም ዘብነት ያሳየ ነው

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

አዲስ አበባ፡- ሕዝባዊና ሃይማኖታዊ በዓላት በፍፁም ሠላማዊ ሁኔታ መጠናቀቃቸው የሕዝቡን ጠንካራ የሠላም ዘብነት ያሳየ ነው ሲል የመንግሥት ኮሙኒኬሽን አገልግሎት ገለፀ::

የመንግሥት ኮሙኒኬሽን አገልግሎት ትናንት ባወጣው መግለጫ እንዳለው፤ በመስከረም ወር ኢትዮጵያ አምራ የታየችባቸው ሕዝባዊ እና ኃይማኖታዊ በዓላት በድምቀትና በሰከነ ሁኔታ ተከብረዋል:: ለበዓላቱ በድምቀትና በሰላም መከበር መላው ሕዝብ እንደወትሮው ሁሉ የላቀ አስተዋፅዖ አበርክቷል፤ ለዚህም ከፍ ያለ ምስጋና ይገባዋል::

የአዲስ ዓመት አቀባበል ከዋዜማው ጀምሮ፤ የመስቀል በዓል፣ ኢሬቻ እና የግሸን ደብረ ከርቤ በዓላት፣ በደቡባዊ ኢትዮጵያ የተለያዩ ክልሎችና ዞኖች የተከበሩ በዓላትም ጭምር ያለምንም የፀጥታ ችግር በሚሊዮኖች በሚቆጠር ሕዝብና በርካታ ቱሪስቶች ተሳትፈውባቸው ሃይማኖታዊ እና ባህላዊ ይዘታቸውን ጠብቀውና በታላላቅ ፈጠራ ታጅበው በድምቀት መከበራቸውንም በመግለጫው አውስቷል::

በዓላቱን ለማክበር ወደ ተለያዩ የአገሪቱ አካባቢዎች የተጓዙ ወገኖቹን ሕዝቡ በፍፁም ኢትዮጵያዊ ፍቅር ተቀብሎ ማስተናገዱም ተመላክቷል::

የፌዴራል እና የክልል የፀጥታ ኃይሎችም ከሕዝቡ ጋር በብቃት ያከናወኑት የሰላምና የደኅንነት ሥራ፤ በዓላቱን ተጠቅመው ጥፋት አስበው የነበሩ የሽብር ቡድኖች እቅድ እንዲከሽፍ አድርጓል ብሏል::

የሚዲያ ተቋማትም የበዓላቱን ድምቀት በማስተጋባት አገራዊ አንድነት እንዲጠናከር፣ የአገር ውስጥ ቱሪዝምና የሥራ ፈጠራ እንዲስፋፋ ከፍተኛ የማነቃቃት ሥራ ሠርተዋል ነው ያለው::

የወርሃ መስከረም በዓላት በድምቀትና በፍጹም ሰላም ተከብረው መጠናቀቃቸው አገራችን በፈተና ውስጥም ሆና ውጤታማ ተግባራትን ማከናወን እንደምትችል ያረጋገጠና የኢትዮጵያውያንንም የአብሮነት እሴት ዳግም በተግባር ያስመሰከረ መሆኑን በመግለጫው ተገልጿል::

በዓላቱ በሰላም እና በድምቀት እንዲከበሩ አስተዋፅዖ ላበረከተው መላው ሕዝብ፣ በየደረጃው ያሉ የፀጥታ አካላት እና የመንግሥት መዋቅሮች፣ ለኃይማኖት አባቶች፣ ለአገር ሽማግሌዎች፣ ለወጣቶችና ለሚዲያ ተቋማት በሙሉ መንግሥት ከፍ ያለ ምስጋና እንደሚያቀርብ ነው ያስታወቀው::

# የአሸባሪው ሸኔ ምክትል አዛዥን ጨምሮ 138 የቡድኑ አመራሮችና አባላት ተማረኩ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

አዲስ አበባ፡- በኦሮሚያ ክልል ምሥራቅ ጉጂ ዞን የሸኔ ቡድን የደቡብ ቀጣና ምክትል አዛዥን ጨምሮ 138 በተለያየ ደረጃ የሚገኙ አመራሮችና አባላት ተማረኩ።

ቡድኑ ለሕዝብ ጥቅም እሠራለሁ ከሚለው የማደናገሪያ ሃሳቡ በተቃራኒ የቆመና የሕዝቦችን ስቃይ የሚያረዝም ሽብርተኛ ኃይል እየሆነ መምጣቱ ወደ መበታተን ደረጃ እያደረሰው መሆኑን ምርኮኞቹ ተናግረዋል።

ከምርኮኞቹ አንዱ የሆነው የታጣቂ ኃይሉ የደቡብ ቀጣና ምክትል አዛዥ አቶ መሃመድ አሜ ከዓመታት በፊት በአገራችን የተዘረጋውን የሰላም አማራጭ እንደመልካም አጋጣሚ በመጠቀም ወደአገር መግባቱንና ለአገር የሚበጅ ተግባር ለመፈፀም ትልም እንደነበረው ተናግሯል።

ምርኮኞቹ፣ የሸኔ የሽብር ቡድን የምንታገለው ለኦሮሞ ሕዝቦች ነፃነት ነው በሚል ወጣቱን ኃይል በማደናገር ብዙዎችን ያሳሳተ የእኩይ አላማ ስብስብ መሆኑን ተናግረዋል።

አሁን መንግሥትና የፀጥታ ተቋማት እየወሰዱት ያለው የተጠናከረ ዘመቻ ከሸኔ ውስጣዊ ችግሮች ጋር ተዳምሮ ቡድኑ የለየለት አቅም ማነስ ውስጥ እንደሚገኝ የሚናገሩት ምርኮኞቹ፤ በቡድኑ ውስጥ ያሉ ወጣቶችም እጃቸውን ለፀጥታ ተቋማት በመስጠት ራሳቸውን እንዲያድኑ ጥሪ አቅርበዋል።



**በቁጥጥር ስር ከዋሉ የጦር መሳርያዎች በከፊል**

የደቡብ ዕዝ የኋላ ደጀን አስተባባሪ ኮሎኔል ግርማ አየለ በበኩላቸው የፀጥታ ግብረኃይሉ መላውን ኅብረተሰብ በማሳተፍ እየወሰደው ባለው እርምጃ የሽብርተኛው የሸኔ ታጣቂ ቡድን አባላት በየዕለቱ እጃቸውን በመስጠት ላይ እንደሚገኙ መናገራቸውን የዘገበው ኢቢሲ ነው።

# በአሸባሪው ትህነግ የወደሙ ተቋማትን መልሶ ለመገንባት መረባረብ ይገባል

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

ደሴ፡- በአሸባሪው ትህነግ የወደሙ ተቋማትን ከቀደመው በተሻለ መልሶ ለመገንባት በሚደረገው የተቀናጀ ጥረት ሁሉም ድጋፍ ማድረግ እንዳለበት የከተማና መሠረተ ልማት ሚኒስትር ጫልቱ ሳኒ አሳሰቡ።

በምሥራቅ አማራ በሽብር ቡድኑ ውድመት ደርሶባቸው በ150 ሚሊዮን ብር ወጪ መልሰው የተገነቡት ተቋማት የፌዴራልና የክልል አመራሮች በተገኙበት የምረቃ ሥነ ሥርዓት መካሄዱን የኢዜአ ዘገባ አመልክቷል፡፡

ሚኒስትሯ በኮምቦልቻ ከተማ መልሰው የተገነቡትን ተቋማት ሲመርቁ እንዳሉት ቡድኑ ኢትዮጵያን ለማፍረስ የወጠነውን ሴራ ለማሳካት በአካባቢው ወረራ በፈጸመበት ወቅት በየከተሞች የሕዝብ መገልገያ ተቋማት ላይ ዘረፋና ውድመት ማድረሱን አስታውሰዋል።

መንግሥት የተለያዩ የኅብረተሰብ ክፍሎችንና ተቋማትን በማስተባበር ተቋማቱን በተሻለ ደረጃ መልሶ ለመገንባት እየሠራ መሆኑን ጠቁመው፤ ለዚህም የሚመለከተው ሁሉ በሚችለው አቅም ማገዝና መደገፍ እንዳለበት አሳስበዋል።

በምሥራቅ አማራ በሰባት ከተሞች በሕወሓት የሽብር ቡድን የወደሙ 18 የማህበራዊ አገልግሎት መስጫ ተቋማት በ150 ሚሊዮን ብር ወጪ መልሶ በመገንባት ለአገልግሎት ክፍት እንዲሆኑ መደረጉም ተገልጿል።

መልሰው ከተገነቡ የማህበራዊ አገልግሎት መስጫ ተቋማት መካከልም 8 ትምህርት ቤቶች፣ 7 የአንድ ማዕከል አገልግሎት መስጫ ተቋማትና 3 ጤና ጣቢያዎች ይገኙበታል።



**ወይዘሮ ጫልቱ ሳኒ**

ተቋማቱን መልሶ ለመገንባት በጀቱ በኢትዮጵያ መንግሥትና በዓለም ባንክ የተሸፈነ መሆኑን አመልክተዋል።

የተቋማቱ አራት ወር ባልሞላ ጊዜ ውስጥ ጥራታቸውን በጠበቀ መልኩ ተገንብተው በመጠናቀቃቸው ያደነቁት ሚኒስትሯ፤ በውላቸው መሠረት ግንባታውን በወቅቱ ያጠናቀቁትን የአማራ ክልል የመንግሥት የልማት ድርጅቶች አመስግነዋል።

መልሰው በተገነቡ ተቋማት ፈጣንና ቀልጣፋ አገልግሎት በመስጠት ሕዝብን በቅንነት ማገልገል እንደሚገባም አስገንዝበዋል።

አንድነታችንና ሰላማችንን ጠብቀን የሽብር ቡድኑን ከመመከት ጎን ለጎን የወደሙ ተቋማትን መልሶ የመገንባት ሥራ አጠናክረን እንቀጥላለን ሲሉም አስታውቀዋል።

የኮምቦልቻ ከተማ ከንቲባ አቶ መሃመድ አሚን የሱፍ በከተማው በሽብር ቡድኑ ከ10 ነጥብ 3 ቢሊዮን ብር በላይ የሚገመት ሀብት መውደሙን ተናግረዋል።

የወደሙ ተቋማትን በቁጭት መልሶ የማቋቋምና የማደራጀት ሥራ በቅንጅት እየተከናወነ መሆኑንም ተናግረዋል።

# ማረሚያ ቤቶች የታራሚዎችን ሰብአዊ ክብር የሚጠብቁና በሙያ አቅም የሚገነቡ መሆን አለባቸው

**ሞገስ ጸጋዬ**

አዲስ አበባ፡- በፌዴራልና በክልል ደረጃ ያሉ ማረሚያ ቤቶች የታራሚዎችን ሰብአዊ ክብር የሚጠብቁ፣ ታራሚዎችን በሙያ የሚያስታጥቁ፣ እውቀት እንዲገበዩ የሚያግዙ፣ በተግባር ስልጠና የሚሰጡ መሆን እንዳለባቸው የፍትሕ ሚኒስትሩ አስታወቁ።

የፌዴራል ማረሚያ ቤት ኮሚሽን በሕግ ማስከበር ዘመቻና በሥራ አፈፃፀም የላቀ ተግባር ለፈፀሙ የተቋሙ አመራር፣ አባላትና ሠራተኞች የማበረታቻና የዕውቅና መርሐ ግብር አከናውኗል።

በመርሐ ግብሩ ላይ የተገኙት የፍትሕ ሚኒስትሩ ዶክተር ጌዲዮን ጢሞቲዮስ እንደገለጹት፤ ማረሚያ ቤቶች የማስተማርና የልማት ሥራ የሚሠሩ በመሆናቸው ከተለያዩ የፌዴራልና የክልል ተቋማት ጋር በቅንጅት መሥራት አለባቸው።

የአንድን ማኅበረሰብ እሴትና ያለበት ደረጃ ለማወቅ ከሚያስችሉ ነገሮች አንዱ ማረሚያ ቤቶች ናቸው ያሉት ዶክተር ጌዲዮን፤ ስለዚህ በፌዴራልና በክልል ደረጃ ያሉ ማረሚያ ቤቶች የታራሚዎችን ሰብአዊ ክብር የሚጠብቁ፣ ታራሚዎችን በሙያ የሚያስታጥቁ፣ እውቀት እንዲገበዩ የሚያግዙ፣ በተግባር ስልጠና የሚሰጡ፣ በግብርናና በእርሻ ልማት የሚያሳትፉ መሆን አለባቸው ብለዋል።

ማረሚያ ቤትን የእውነት ማረሚያ ቤት ማድረግ ያስፈልጋል ያሉት ሚኒስትሩ፤ ጠንክሮ በመስራት የትምህርት፣ የስልጠናና የምርት ማዕከል መሆን አለባቸው ብለዋል።

እንደ ዶክተር ጌዲዮን ገለጻ፤ ማረሚያ ቤቶች ሲባል ዜጎች የሚታረሙበት፣ በትምህርት ራሳቸውን የሚያንጹበትና የሚገነቡበት፣ አምራች ዜጋ መሆንን የሚለማመዱበት ማዕከላት መሆኑን ሰዎች ሊገነዘቡ ይገባል። አንድ አገር ጥፋተኛ ናቸው፣ ወንጀል ሠርተው በድለውኛል የምትላቸውን ዜጎች እንዴት ነው የምትንከባከባቸው? ሰብአዊ መብታቸውና ክብራቸው ይከበራል ወይ፤ አምራች ዜጋ እንዲሆኑ ምን አገልግሎት ያገኛሉ የሚለው ወሳኝ በመሆኑ የፌዴራል ማረሚያ ቤት ከጊዜ ወደ ጊዜ እየዘመነና እየተሻሻለ መሄድ አለበት። የሚሰጣቸው የጤናና የትምህርት አገልግሎቶችም ተጠናክረው ሊቀጥሉ ይገባል።



ለአትሌት ኮማንደር ደራርቱ ቱሉ የምኮሚሽነርነት ማዕረግ ተሰጥቷል

ወደፊት ታራሚዎች እንደጥፋታቸውና እንደ ዕድሜያቸው ደረጃ ከእስር በተጨማሪ ትምህርትና የማህበረሰብ አገልግሎትን በመጠቀም በአማራጭ መንገዶች የማረም ሥራን ለማገዝ ከፍተኛ እንቅስቃሴ ይደረጋል ያሉት ዶክተር ጌዲዮን፤ ወንጀል የሠሩ ቢሆንም ሊያርማቸው የሚችለው አካሄድ የማረሚያና የማነጫ ስልቱ የተለያየ ሊሆን ስለሚችል በእስር ብቻ ማረም ላይቻል ይችላል። ስለዚህ ዘመናዊ አስተሳሰብን በመከተል በብዙ ባለሙያዎች የሚታመንበትን የማረሚያ ስልቶችን አማራጭ በአዲስ የሕግ ማዕቀፍ ተግባራዊ ለማድረግ በቅርቡ ብዙ እንቅስቃሴዎች ይኖራሉ ብለዋል።

የፌዴራል ማረሚያ ቤት ኮሚሽን ኮሚሽነር ጄኔራል አቶ ዳመነ ዳሮታ በመርሐግብሩ እንደገለጹት፤ ኮሚሽኑ በፍርድ ቤት ውሳኔ የሚላኩ ታራሚዎችን በመንከባከብ የአስተሳሰብ ለውጥ አምጥተው አምራች ዜጋ እንዲሆኑ እየተሠራ ነው።

ለዚህም አሳሪ የሆኑ ሕጐች ተቀይረዋል። ታራሚዎች በሚታረሙበት ወቅት የተለያዩ የሙያ ልምዶችን ይማራሉ፤ ዘመናዊ ማረሚያ ቤት እንዲሆን ከፍተኛ ጥረት እየተደረገ ነው። ለዘመናት የኮሚሽኑ ችግር የነበረው የመኪና ችግር የተቀረፈ በመሆኑ ኮሚሽኑ ሥራውን በተገቢው ሁኔታ እየሠራ ነው ሲሉም ጠቁመዋል።

ኮሚሽኑ ለኮማንደር አትሌት ደራርቱ ቱሉና ለኮማንደር አሰልጣኝ ሁሴን ሼቦ ልዩ ተሸላሚዎች በማድረግ የምክትል ረዳት ኮሚሽነርነት ማዕረግ ሰጥቷቸዋል። ለተቋሙ አመራሮችና ሠራተኞችም ማበረታቻና ዕውቅና ሰጥቷል፤ እንዲሁም በሕግ ማስከበር ዘመቻ ወቅት ሥራቸውን በከፍተኛ ውጤት ለተወጡ አመራሮች የማዕረግ እድገት ሰጥቷል።

# ሁከት ሊቀሰቅሱ የነበሩ 166 የሽብር ቡድን አባላት በቁጥጥር ስር ዋሉ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

አዲስ አበባ፡- በመስቀል የደመራ ሥነሥርዓት እንዲሁም በአዲስ አበባ እና በቢሾፍቱ በተከበረው የኢሬቻ በዓል ላይ የሽብር ተግባር በመፈጸም አገራዊ ቀውስ እንዲፈጠር በህቡዕ ሲያሴሩ የነበሩ ተጠርጣሪዎች በቁጥጥር ስር ውለው ምርመራ እየተካሄደባቸው መሆኑን የጸጥታና ደኅንነት የጋራ ግብረኃይል አስታውቋል።

የጸጥታና ደኅንነት የጋራ ግብረኃይል ለመገናኛ ብዙኃን በላከው መግለጫ እንዳስታወቀው፤ አሸባሪ ቡድኖች በመስከረም ወር በሚከበሩት የአደባባይ በዓላት ላይ ሁከትና ብጥብጥ በመቀስቀስ አገራዊ ይዘት ወዳለው ቀውስ እንዲሸጋገር በህቡዕ ሴራ ሲጠነስሱ ነበር። ይሁንና የጸጥታና ደኅንነት የጋራ ግብረኃይል የአደባባይ በዓላቱ ሰላማዊ ሆነው እንዲጠናቀቁ ባደረገው ጠንካራ ቅድመ ዝግጅትና ምስጢራዊ ክትትል ሴራውን ከውጥኑ ማክሸፍ ተችሏል። በዚህም 166 የሕወሓት፣ የሸኔ፣ የአይ ኤስ እንዲሁም የኢመደበኛ አደረጃጀት አባላት በቁጥጥር ስር እንዲውሉ ተደርጓል።

የአሸባሪ ቡድኑ አባላት በመስቀል የደመራ ሥነሥርዓት እንዲሁም የኢሬቻ በዓል በሚከበርባቸው አዲስ አበባ እና ቢሾፍቱ ሁከትና ብጥብጥ የመቀስቀስ ተልዕኮ ተቀብለው በህቡዕ ሲንቀሳቀሱ እንደነበር የጠቆመው የጋራ ግብረኃይሉ መግለጫ፤ በተለይ አሸባሪው ሸኔ የሽብር ተግባር የሚፈጽሙ ሴሎችን ሲያደራጅ እና አባ ቶርቤ የተባለውን ገዳይ ቡድን ለማሰማራት ሙከራ ሲያደርግ መቆየቱን ጠቅሷል።

ለዚሁ የጥፋት ተልዕኮውም ከሕወሓት የሽብር ቡድን ጋር በመቀናጀትና የሎጀስቲክስ አቅርቦት በማመቻቸት ዝግጅት ሲያደርግ መቆየቱን አመልክቷል።




የጸጥታና ደኅንነት የጋራ ግብረኃይል በሽብር ቡድኖች እና በተጠርጣሪ ግለሰቦች ህቡዕ እንቅስቃሴና የግንኙነት መረብ ላይ ሲያደርግ በነበረው ምስጢራዊ ክትትልም የአደባባይ በዓላቱን ወደ ቀውስ ለመቀየር ለታቀደው እኩይ ተልዕኮ መፈጸሚያ የሚሆኑ የቡድንና የነፍስ ወከፍ የጦር መሣሪያዎች፣ ተቀጣጣይ ፈንጂዎች፣ ቦምቦች እና በርካታ ጥይቶችን መያዙን ገልጿል።

ተጠርጣሪዎቹ ከአይ ኤስ የሽብር ቡድን ጋር በጋራ እንደሚሠሩና ከአሸባሪው ሕወሓት ተልዕኮ ተቀብለው ሲንቀሳቀሱ እንደነበር የሚያስረዱ የሰነድ ማስረጃዎችም ተገኝተዋል ብሏል።

መላው የጸጥታና ደኅንነት አካላት ተልዕኳቸውን በቁርጠኝነት ለመወጣት ቀን ከሌት መሥራታቸው እንዲሁም የኅብረተሰቡም የነቃ ተሳትፎ የታቀደው የሽብር ተግባር እንዲከሽፍ ከፍተኛ አስተዋጽዖ ማበርከቱን ያመለከተው መግለጫው፤ በዘመን መለወጫ ወቅት የሚከበሩት የአደባባይ በዓላት የመላው ኢትዮጵያውያን የአብሮነት እሴት መገለጫና የጋራ ሀብት ናቸው፤ በርካታ ቱሪስቶችም የሚታደሙባቸው በመሆናቸው ተገቢው ጥበቃ ይደረግላቸዋል እንጂ የአንዳንድ የውጭና የውስጥ ፀረ-ሰላም አካላት አጀንዳ ማስፈጸሚያ አይሆኑም ብሏል።

በዓላቱ ሰላማዊ ድባብ የሰፈነባቸው እንዲሆኑ መላው ኅብረተሰብ ላሳየው ከፍተኛ ተሳትፎም የጸጥታና ደኅንነት የጋራ ግብረኃይል ልባዊ ምስጋናውን አቅርቧል።

# የውጭ ኃይሎች ጣልቃገብነት ተገቢ አለመሆኑን መንግሥት ለሚመለከታቸው አካላት በየጊዜው ሊያሳውቅ ይገባል

**ውብሸት ሰንደቁ**

አዲስ አበባ፡- የኢትዮጵያ መንግሥት በተለያዩ የውጭ ኃይሎች የሚደረግበት የፖለቲካ ጣልቃ ገብነት ተገቢነት የሌለው መሆኑን በማሳየት ያለውን አቋም በተደጋጋሚ ለየአገራቱ እና ለተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ሊያሳውቅ እንደሚገባ ተገለፀ፡፡ ከሰሞኑ እየተካሄደ በሚገኘው የመንግሥታቱ ድርጅት ስብሰባ ላይ የኢትዮጵያ መንግሥት በወሳኝ ጉዳዮች ላይ ያለውን አቋም አሳውቋል፡፡

በባህርዳር ዩኒቨርሲቲ የፖለቲካል ሳይንስና ዓለም አቀፍ ጥናት ትምህርት ክፍል መምህርና ተመራማሪ ረዳት ፕሮሰፌር ያየሁ ገነት እንደሚሉት፤ መንግሥት ለተባበሩት መንግሥታት ድርጅትም ሆነ ለተለያዩ አገራት በሰሜኑ ክፍል ያለውን ጦርነት አስመልክቶ ያለውን አቋም ማሳወቁ ተገቢነት ያለው ነው፡፡

መንግሥት የተለያዩ መግለጫዎች እስኪወጡ እና ጫናዎች እስኪመጡ ድረስ ሳይጠብቅ ጦርነቱን በሰላም ለመፍታት ያለውን አቋም ማሳወቅ አለበት ያሉት አቶ ያየሁ፤ ጦርነቱ አፍሪካዊ መፍትሄ ሊሰጠው እንደሚገባና ወደ ሰላም መሄድ አማራጭ የሌለው ምርጫ መሆኑን ጠቁመዋል፡፡ ሆኖም በተባበሩት መንግሥታት ድርጅት እና በአንዳንድ አገራት አሸባሪው ሕወሓትን ሕጋዊ ሰውነት እንዳለው አካል የመቁጠር አዝማሚያ አለ ብለዋል፡፡

በተጨማሪም በሰሜኑ የአገሪቱ ክፍል ባለው ጦርነት በሰብዓዊ መብት ጥሰት ሰበብ የኢትዮጵያን መንግሥት እጅ ለመጠምዘዝ የሚደረጉ ፖለቲካዊ ጣልቃ ገብነቶች በተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ዘንድ ተንፀባርቋል፡፡

ስለዚህም የኢትዮጵያ መንግሥት በተለያዩ አካላት የሚደረግበት የፖለቲካ ጣልቃ ገብነት ተገቢነት የሌለው መሆኑን በማሳየት ያለውን አቋም በተደጋጋሚ ለየአገራቱ እና ለተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ሊያሳውቅ ይገባል ብለዋል ረዳት ፕሮፌሰሩ፡፡

በሌላ በኩል የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት አሸባሪው ሕወሓትን ሕጋዊ ሰውነት እንዳለው አካል በመቁጠር ግንኙነት ያደርጋል ያሉት ረዳት ፕሮፌሰር ያየሁ፤ እንደዚህ ዓይነት ግንኙነቶች ስህተት ናቸው ብለዋል፡፡

ከአሸባሪው ሕወሓት ጋር የሚደረግ ግንኙነት ቡድኑ ዓለም አቀፍ ሕጋዊ ሰውነት የሌለው በመሆኑ ውድቅ የሚሆን ነው ሲሉም አክለዋል፡፡

በተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ጠቅላላ ጉባዔ ውስጥ ኢትዮጵያ ዓለም አቀፍ ሕጋዊ ሰውነት ያላት አገር በመሆኗ ተ.መ.ድ ከአሸባሪው ትሕነግ ጋር ግንኙነት መፍጠር የሚያስችለው ምንም ዓይነት መርሕም ሆነ ዓለም አቀፍ ሕግ የለም ብለዋል፡፡

በመሆኑም የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ከአሸባሪ ቡድን ይልቅ ብዙ መረጃዎችን መስማት እና መውሰድ እንዲሁም ትብብር ማድረግ ያለበት ከኢትዮጵያ መንግሥት ጋር ነው ሲሉ ገልፀዋል፡፡

በአንዲት ሉአላዊ አገር በመንግሥትና በሸማቂ ኃይሎች መካከል በሚደረግ ጦርነት የትኛውም አገርም ሆነ ዓለም አቀፍ ድርጅት ጣልቃ መግባት እንደማይችል ሊታወቅ ይገባልም፤ የኢትዮጵያ መንግሥትም ሉአላዊነቱን በተጠና የዲፕሎማሲ አካሄድ ሊያስከብር ይገባል ሲሉ ተናግረዋል፡፡

መንግሥት በዲፕሎማሲው ረገድም ከተለያዩ አገራት ጋር እያደረገ ያለው ግንኙነት መልካም መሆኑን አንስተው የሚደረጉ የዲፕሎማሲ ግንኙነቶች ብሔራዊ ጥቅምን ባስከበረ መልኩ ሊቀጥሉ እንደሚገባ ጠቁመዋል፡፡

# አሸባሪዎቹ ትህነግ እና ሸኔ አገርን ለማፍረስ ከአልሸባብ ጋር በትብብር ይሠራሉ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

አዲስ አበባ፡- አሸባሪዎቹ ትህነግ እና ሸኔ ከዓለም አቀፍ አሸባሪው ጋር እየተናበቡ ኢትዮጵያን ለማፍረስ የሚያደርጉት ድርጊት አንድነታቸውን እንደሚያሳይ የአምቦ ዩኒቨርሲቲ መምህር አሰታወቁ።

በዩኒቨርሲቲው ፖለቲካል ሳይንስ መምህር ሰለሞን ተፈራ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፣ ዓለም አቀፍ አሸባሪው አልሸባብ አሸባሪዎቹ ሕወሓትና ሸኔ ኢትዮጵያን ለማፍረስ የሚያደርጉት ድርጊት እንደመልካም አጋጣሚ መጠቀም የሽብርተኛ ቡድኖች አንድነት መገለጫ ነው።

አልሸባብ በሰሜን በኩል አሸባሪው ሕወሓት ጦርት ሲከፍት በምሥራቅ በኩል ደግሞ በሶማሌ ክልል ኢትዮጵያን የማፍረስ ሥራ እንዲሠራ አልሸባብ ተልዕኮ ወስዶ ሲሠራ መቆየቱን ጥናቶች እንደሚያሣዩም ገልጸዋል።

አሁን ባለው ነባራዊ ሁኔታ ሁለቱም አሸባሪ ቡድኖች እየተናበቡ ኢትዮጵያን የማፍረስ አካሄድ ይታይባቸዋል። ለዚህም በቅርብ ጊዜ የአልሸባብ ሙከራን ማንሳት ይቻላል ብለዋል።

እንደ አቶ ሰለሞን ገለጻ የራሳቸውን ፍላጎት በኢትዮጵያ ላይ ለመጫን የሚፈልጉ አካላት ከትግራይ የሚወጣውን የተሳሳተ መረጃ መሠረት በማድረግ አገርን ጫና ውስጥ መክተት ይፈልጋሉ። በተለይ የአንዳንድ



መምህር ሰለሞን ተፈራ

ምዕራባውያን ወዳጅ የሆኑ አገራትና እነሱን ማዕከል ያደረጉ ተቋማት በተገኘው አጋጣሚ ኢትዮጵያን ለማዳከም ሁሌም የሚያደርጉት ሴራ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ የመናበብ ሁኔታዎች ይታይባቸዋል።

ይህም ብቻ ሳይሆን እነዚህ ኃይሎች ከማይፈልጓቸው አገራት ጋር ኢትዮጵያ ግንኙነነት እንዳትፈጥር የርዕዮተዓለም ጦርነት በማካሄድ ላይ ይገኛሉ። አንዳንድ ምዕራባውያን ፍላጎታቸውን ለማስፈጸም በእነሱ የሚዘወሩ ዓለም አቀፍ ተቋማት በተዘዋዋሪ ለኢትዮጵያ በጎ ምላሽ የማይሠጡበት አጋጣሚዎችን ይፈጥራሉ። አገር ውስጥና ዓለምአቀፍ አሸባሪ ቡድኖች በመናበብ በተመሳሳይ ጫና በመፍጠር አገር ለማፍረስ ይጥራሉ ብለዋል።

አሸባሪው ሕወሓት በመንግሥት የተዘረጉ የሰላም እጆችን ወደ ጎን በመተው ከሌሎች አሸባሪ ኃይሎች ጋር እየተናበበ አገር የማፍረስ ድርጊት የመረጠበት ምክንያት እስከ አሁን ድረስ ከፈፀማቸው ወንጀሎች ተጠያቂነት ለማምለጥ ነው። አሁንም ቢሆን በተሳሳተ መረጃ ዓለም አቀፍ ኅብረተሰብን በማደናገር በትግራይ አባቶችና ወጣቶች ዕድሜውን ለማራዘም ጥረት ላይ ነው ሲሉም ተናግረዋል።

አሸባሪው ሕወሓት ከባሕሪው አንጻር ሠላም የማይፈልግ ስብስብ በመሆኑ በመከላከያው ኃይል ተገዶ ወደ ሠላም አማራጭ መምጣት እንዳለበት ገልጸው መከላከያውም የኢትዮጵያን ሉዓላዊ ግዛት የማስጠበቅ ተልዕኮውን በተለመደው መልክ አስተማሪ እርምጃዎቹን ሊቀጥልበት ይገባል ብለዋል።

የትግራይ ሕዝብ ከሕወሓት ፖለቲካ ማጭበርበር እንዲጠነቀቅ መንግሥት ለትግራይ ሕዝብ ግልጽ የሆነ ቃል ሊገባለት ይገባል። ትግራይ የኢትዮጵያ ሉዓላዊ ግዛት መሆኗን ትግራይ ሕዝብ ተገንዝቦ ንጹኃን የትግራይ አባቶች እና እናቶች ከአሸባሪው ተለይቶ የሚታዩበት የፖለቲካ ሥራ መሠራት አለበት። ለትግራይ ሕዝብ የተለገሰውን እርዳታ ለጦር መሣሪያ ግዥ ቡድኑ ሲጠቀምበት እንደነበረ ሕዝቡ ሊረዳ ይገባል ሲሉም አሳስበዋል።

ከዓለም አቀፍ ሽብር ቡድን ጋር እየተናበበ በአማራ እና አፋር ክልል ሴቶች በመድፈር፣ በመግደል፣ ንብረት በማውድም ሽብር እየፈጸመ ያለውን ቡድን ለማስወገድ በሚደረገው ትግል የትግራይ ሕዝብ ከመከላከያ ጎን መቆም እንዳለበትም ገልጸዋል።

መከላከያ ሠራዊቱ በሚቆጣጠርባቸው ቦታዎች መንግሥት በሠላማዊ መንገድ ነገሮችን መፍታት እንደሚፈልግ፣ ለዜጎቹ የቆመ መንግሥት መሆኑን የሚያሳይ ሥራም በተጨባጭ መሠራት አለበት።

መከላከያው ከተቆጣጠረ በኋላ ቦታው የማንኛውም ቡድን ይሁን ከሕግና ሥርዓት ውጪ ይዞ የራስ ከማድረግ ሁሉም ሊቆጠብ እንደሚገባም መክረዋል።

ሚዲያዎችም በጥንቃቄ መዘገብ እንዳለባቸው ገልጸዋል። ሚዲያው መንግሥት ትግራይ ሕዝብን ከአሸባሪው ሕወሓት ለይቶ የሚያይበት አገላለጾች መጠቀም አለባቸው። ዓለም አቀፍ ኅብረተሰብን በማሳሳት በሰብዓዊ እርዳታ ስም ሕወሓት መንሰራራት እንደሚሞክር ገልጸው፣ በቅርቡ ወደ ትግራይ የገባውን ነዳጅ እና ዱቄት ከሕዝብ ጎሮሮ ነጥቆ ለሦስተኛው ዙር ጦርነት እየተጠቀመበት መሆኑን ማስረዳት መቻል አለበት ሲሉም ገልፀዋል።

## የአፈታተን ሥርዓቱ ተማሪዎችን...

**ከ1ኛው ገጽ የዞረ**

በጦርነት ቀጣና የሚገኙ እና አሁን ባለው ሁኔታ ማስፈተን አንችልም ብለው የገለጹ ክልሎችን መሠረት በማድረግ በመጀመሪያ ዙር መልቀቂያ ፈተናን መውሰድ ያልቻሉ 56 ሺ ተፈታኞች በቅርቡ በሁለተኛ ዙር ለመስጠት ዝግጅት መደረጉን ፕሮፌሰር ብርሃኑ ገልጸዋል።

የፈተና አሰጣጥ ሂደቱ ከፈተና ስርቆት፣ ከኩረጃ እና ከሐሰተኛ የፈተና መልስ ስርጭት ነፃ ሆኖ እንዲከናወን ያስችላል፡፡ ተፈታኞቹም በማጥናትና በመሥራት ብቻ አምነው እንዲዘጋጁና የፈተና ሥርዓቱ ተዓማኒነት እንዲያድግ ያግዛል ብለዋል፡፡

የፈተናውን ውጤታማነት ለመጨመር የፈተና ኮዶችን ጭምር ከአራት ወደ 12 ከፍ መደረጉን የገለጹት፤ ሚኒስትሩ፤ ፈታኞቹ ከተለያዩ ዩኒቨርሲቲዎች የተመለመሉ እንደሆነና ሂደቱን ከሰፈርተኝነት አስተሳሰብ ለማላቀቅ ከፍተኛ ጥንቃቄ መደረጉም ተጠቁሟል፡፡

ለፈተናው ዝግጅት የሚወጣው ወጪ የፈተና ሥርዓት ሂደት የሚፈጥረው የሞራል ስብእና እና ከሚፈጠረው አለመተማመን በላይ አይደለም፣ የተመደበው ወጪ ከነበረው ችግር አንጻር አይከብድም ብለዋል፡፡

ፈተና ሲዘጋጅ ሂደትን ጠብቆ ነው፡፡ የራሱ የምዘና ሥርዓት አለው፣ የሚዘጋጁት ፈተናዎችም እኩል የምዘና ሥርዓትን የሚያልፉ ናቸው ሲሉም በመጀመሪያ እና በሁለተኛ ዙር የፈተና አቀራረብ አኳያ ልዩነት እንደማይፈጠር አመልክተዋል፡፡

ለፈተና አፈትልኮ መውጣት ምክንያት የሆኑትን ከፈተና ዝግጅት እና ሕትመት ጋር ተያይዞ የነበሩ ክፍተቶችን ለመሸፈን ከፍተኛ ጥንቃቄ መደረጉንም አመልክተዋል፡፡ ስርጭትን በሚመለከትም ፈተና የሚሰጥባቸው ዩኒቨርሲቲዎች የአውሮፕላን ጣቢያ ባሉባቸው አካባቢዎች እንዲሆኑ በመደረጉ የነበረውን ችግር መቀነስ እንደተቻለም ነው ያብራሩት፡፡

ከአካባቢያቸው የሚንቀሳቀሱ ተፈታኞችን የደህንነት ሁኔታ ክልሎችና የፌዴራል ፖሊስ በቅንጅት እንደሚያከናውኑ የገለጹት ፕሮፌሰር ብርሃኑ፤ አጠቃላይ የጸጥታና ደህንነትን የማረጋገጥ ተግባር በፌዴራል ፖሊስ እንደሚመራ አመልክተዋል፡፡

ተፈታኝ ተማሪዎች ለተደነገጉ የፈተና ደንቦች ተገዢ መሆን አለባቸው፣ በፈተና ወቅት የተከለከሉ ቁሳቁሶችን ይዞ የተገኘ ተማሪ ከፈተና ውጪ ይሆናል ሲሉም ፕሮፌሰር ብርሃኑ፤ አሳስበዋል፡፡

ተማሪዎች፣ የተማሪ ወላጆች፣ የጸጥታ አካላት እና ሁሉም የኅብረተሰብ ክፍሎች ፈተናው ሰላማዊ ሆኖ እንዲጠናቀቅ የበኩላቸውን ሚና እንዲወጡ ጥሪ ያቀረቡት ሚኒስትሩ፤ ማሕበራዊ አንቂዎች የተጀመረውን ሥራ እንዲደግፉም ጥሪ አቅርበዋል፡፡ ብዙኃን መገናኛ ተአማኒነት ያለውን መረጃ ከሚመለከታቸው አካላት ወስደው በማሰራጨት ኃላፊነታቸውን ሊወጡ እንደሚገባም ጠቁመዋል፡፡

የትራንስፖርትና ሎጅስቲክስ ተቋማትና አገልግሎት ሰጪ ማሕበራት እና ባለሀብቶች ተማሪዎች ካሉበት ስፍራ ወደ ተመደቡበት ዩኒቨርሲቲዎች ሲንቀሳቀሱ ተግዳሮትና እክል እንዳይገጥማቸው እንዲተባበሩ ጠይቀዋል፡፡

ዶክተር ፋንታ በበኩላቸው አዲሱ የአፈታተን ሥርዓት ተማሪዎች ተረጋግተው እንዲፈተኑ እንደሚያስችል ጠቁመዋል፡፡ በእውቀታቸው፣ በክህሎታቸው ተለይተው የሚመጥናቸው ቦታ ላይ እንዲመደቡ እንደሚያስችልም ነው የገለጹት፡፡

የአገር አቀፍ ትምህርት ምዘናና ፈተናዎች አገልግሎት ዋና ዳይሬክተር ዶክተር እሸቱ ከበደም የፈተና ሥርዓቱን ማሕበራዊ ሀብት በማድረግ ከፖለቲካ መሣሪያነት ለማላቀቅ ኅብረተሰቡ ተባባሪ ሊሆን እንደሚገባ አሳስበዋል፡፡

የ2014 ዓ.ም ተፈታኞችን ከመስከረም 30 ቀን 2015 ዓ.ም ጀምሮ እና በቅርቡ በሚሰጠው የሁለተኛ ዙር በመፈተን የ2015 ዓ.ም ተፈታኞችን ደግሞ በግንቦት ወር በመፈተን የትምህርት ካሌንደሩን ለማስተካከል መታቀዱንም ፕሮፌሰር ብርሃኑ ጠቁመዋል፡፡

የማህበራዊ ሳይንስ ተፈታኞች ከመስከረም 26 እስከ 28 ወደሚፈተኑባቸው ዩኒቨርሲቲዎች የሚገቡ ሲሆን ከመስከረም 30 እስከ ጥቅምት 02 ፈተና ወስደው ከጥቅምት 03 ጀምሮ ወደመጡበት እንደሚመለሱ ተጠቅሷል።

የሁለተኛ ዙር የተፈጥሮ ሳይንስ ትምህርት ዘርፍ ተማሪዎች ከጥቅምት 08 ቀን እስከ 11 ድረስ ፈተናውን የሚወስዱ ሲሆን፤ ጥቅምት 05 እና 06 ወደ ሚፈተኑበት ዩኒቨርሲቲ እንደሚገቡ ተጠቁሟል፡፡ ፈተናውን ጨርሰው ጥቅምት 13 ቀን 2015 ዓ.ም እንደሚመለሱ ነው የተገለጸው፡፡

የመጀመሪያ ዙር የ2014 ዓ.ም የመልቀቂያ ፈተናን መውሰድ ያልቻሉ ከ56 ሺህ በላይ ተማሪዎች የመጀመሪያው ዙር ፈተና በተጠናቀቀ በአንድ ወር ጊዜ ለመስጠት ዝግጅት መደረጉን ገልጸዋል።

## «መንግሥት ረሃብን...

**ከ1ኛው ገጽ የዞረ**

ኮማንደር ገ/መስቀል ለኢፕድ ጋዜጣ እንደተናገሩት፤ መንግሥት ረሃብን እንደ ጦር መሣሪያ አድርጎ ተጠቅሟል ማለት ከእውነት የራቀ ሆን ብሎ የተፈበረከ የፖለቲካ ሽፍጥ ነው፤ እውነታው ግን ማስረጃ ስላለ የሚረጋገጥ ጉዳይ ነው ብለዋል።

ሰብአዊ እርዳታ ወደ ትግራይ እንዳይገባ በተደጋጋሚ ጦርነት በመክፈት ሲያደናቅፍ የነበረው አሸባሪ የሕወሓት ቡድን ሆኖ እያለ፤ ኮሚሽኑ የፌዴራል መንግሥት ረሃብን እንደ የጦር መሣሪያ አድርጎ ተጠቅሞበታል ማለቱ ከእውነት የራቀ ብቻ ሳይሆን ሆን ብሎ መንግሥትን ለመወንጀል የተሴረ አካሄድ ነው ብለዋል።

የተባበሩት መንግሥታት የሰብአዊ መብት ባለሙያዎች ኮሚሽን ዓለም አቀፉን ማህበረሰብ በማሳሳት የአንዳንድ የውጭ ኃይሎችን ፖለቲካዊ አላማ ለማሳካት ካልሆነ በስተቀር የፌዴራል መንግሥት ሰብአዊ እርዳታ ወደ ትግራይ ከመላክ ወደ ኋላ ብሎ አያውቅም ብለዋል።

«ኮሚሽኑ አሸባሪ የሕወሓት ቡድን ዓለም አቀፉን ማህበረሰብ ሆን ብሎ ለማሳሳት የሚያደርገውን ጥረት መደገፉ ያሳዝናል» ያሉት ኮማንደር ገብረመስቀል፤ የፌዴራል መንግሥት ሕዝቡ እንዳይራብ በማሰብ የሚችለውን ሁሉ ዋጋ እየከፈለ እርዳታ ሲልክ ነበር፤ ይህንንም የዓለም ማህበረሰብ ያውቀዋል ሲሉ ገልጸዋል፡፡

ቡድኑ የፌዴራል መንግሥት የሰብአዊ እርዳታ እንዳይገባ እያደናቀፈ ነው በማለት የውሸት ፕሮፓጋንዳ ቢነዛም በተግባር ግን መንገድ እየዘጋ የነበረው ራሱ አሸባሪው ቡድን ነው ሲሉ ገልጸዋል።

ቡድኑ የትግራይ ሕዝብ በፌዴራል መንግሥት ላይ ጥላቻ እንዲያሳድር የሀሰት የፖለቲካ ፕሮፓጋንዳ እየነዛ ይገኛል ያሉት ኮማንደሩ፤ በአፉ እርዳታ መግባት አለበት እያለ በተግባር ግን እያደናቀፈ ያለ መሆኑን ዓለም አቀፉ ማህበረሰብ ሊገነዘብ ይገባል ሲሉ ተናግረዋል።

## ሚኒስቴሩና ተጠሪ ...

**ከ1ኛው ገጽ የዞረ**

አብዛኛዎቹ የኢንዱስትሪ ምርቶች ለሠራዊቱ የሚጠቅሙ በመሆናቸው በቀጣይ በምርቶቹ ላይ ሰፊ ትኩረት ተሰጥቶ እንደሚሠራባቸው ተናግረው፤ የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር የኢትዮጵያን እድገትና የብልጽግና ጉዞ ለማሳካት የሚያደርገውን ጥረት አጠናክሮ እንዲቀጥል አሳስበዋል።

የኢንዱስትሪ ሚኒስቴርና ተጠሪ ተቋማቱ ላደረጉት ድጋፍ አመስግነው የተደረገው የገንዘብና የዓይነት ድጋፍ ለሠራዊቱ የሞራል ስንቅ ይሆናል ብለዋል።

የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር የሠራዊቱን ልብስ በአገር ውስጥ ለማምረት የሚያደርገው ጥረት የሚደነቅ ነው ያሉት ሚኒስትሯ፤ ለመከላከያ ሠራዊት የሚደረገው ድጋፍ እንዲጠናከር ጥሪ አቅርበዋል።

## የአደባባይ በዓላት...

**ከ1ኛው ገጽ የዞረ**

ባህል፣ እሴትና አለባበስን በሂደት የሚሸረሽሩ ናቸው። ባህልና እሴት ደግሞ የማህበረሰብ መለያ በመሆናቸው ለቱሪዝም እድገት የበኩላቸውን አስተዋጽዖ ያደርጋሉ።

የአንድ ማህበረሰብ ባህል ከሌሎች የማህበረሰብ ክፍሎች የሚለይበት የራሱ የሆነ መለያና የአከባበር ሥነ ሥርዓት ያለው በመሆኑ ማህበረሰቡን ከሌሎች ማህበረሰብ ውብ ሆኖ እንዲታይ ያደርገዋል ያለው ጋዜጠኛ ሄኖክ፣ የአደባባይ በዓል ያላቸው ማህበረሰቦች ልዩ የሚያደርጋቸውን ውበት መጠበቅ አለባቸው ብሏል።

የአደባባይ በዓል የሚያከብሩ ሕዝቦች የአከባበሩን ሥነ ሥርዓት ከሚያበላሹ ድርጊቶች ባህላቸውን መጠበቅ አለባቸው ያለው ጋዜጠኛ ሄኖክ፤ የበዓላቱ የአከባበር ሥነ ሥርዓት መቀየር የቱሪዝም ዘርፉን እንዲዳከምና እንዲጠፋ ያደርገዋል፤ ልዩነት ውበት እንደመሆኑ መጠን ልንከባከበውና ልንጠብቀው ይገባል ሲል ተናግሯል።

ኢትዮጵያ በተፈጥሮ ለቱሪዝም የምትመች አገር እንደመሆኗ መጠን የዘርፉን እድገት የሚያቀጭጩ ጉዳዮችን በቶሎ መፍታት ያስፈልጋል ያለው ጋዜጠኛ ሄኖክ፣ በሰሜኑ የአገራችን ክፍል የዚህ ምክንያት አካል እንዳይሆን በቶሎ መፍትሄ ሊያገኝ ይገባል ብሏል።

እንደ ጋዜጠኛ ሄኖክ ገለጻ፤ የቱሪዝም ዘርፉን ለማሳደግ በመንግሥት በኩል በርካታ ጥረቶች እየተደረጉ ቢገኝም በቂ አይደለም። ምክንያቱም ዘርፉን ለማሳደግ ኢትዮጵያ በዓለም ቅርስነት ከተመዘገቡት ውጪ በርካታ ክብረ በዓላትና ተፈጥሮን ድንቅ የሚያስብሉ ፏፏቴዎች፣ ዋሻዎች እንዲሁም እንስሳትና ብርቅዬ ወፎች ያሏት አገር ናት።

ስለዚህ የቱሪዝም ዘርፉን ለማሳደግ ዓለም ከሚያውቃቸው የአደባባይ በዓላት በተጨማሪ የማይታወቁትን የአከባበር ሥነ ሥርዓቶችን በሰፊው ማስተዋወቅ ያስፈልጋል ብሏል።

እንደ ጋዜጠኛው ገለጻ፣ ከተለያዩ የአለም አገራት የሚመጡ ቱሪስቶችን ለማስተናገድ የሚያስችሉ መሠረተ ልማቶችን ማዘጋጀት የመንግሥት ኃላፊነት ነው። በአገሪቷ ያሉት ተፈጥሮና ባህል በሁሉም አቅጣጫ የሚተዋወቁ ከሆነና እንግዳ የመቀበል አቅም የሚያድግ ከሆነ ኢትዮጵያ እንደአገር በቱሪዝም ዘርፍ ከዓለም አገራት ቁጥር አንድ የማትሆንበት ምክንያት የለም።

በኢትዮጵያ አደባባይ በዓላት የሚገለጡት ቁሳቁስ፣ አልባሳትና ጌጣጌጥ ከሌሎች አገራት ባህል፣ አለባበስና አከባበር አንጻር የተሻለና የተለየ ነው ያለው ጋዜጠኛ ሄኖክ፣ የኢትዮጵያ የአደባባይ በዓላት የሚያሸበርቁት ኢትዮጵያ ውስጥ ባሉ ቁሳቁስ፣ ግብዓትና በማህበረሰቡ በእጅ የተሠሩ አልባሳትና ጌጣጌጥ በመሆኑ ነው ብሏል።

በሌሎች አገራት የሚከበሩ የአደባባይ በዓላት መድመቂያቸውን ከሌላ አካባቢ በሚመጡ ጌጣ ጌጦች የሚያሽቆጠቆጡ በመሆናቸው ከኢትዮጵያ ኪነ ጥበብ አንጻር ውበታቸው ደካማ ነው። ስለዚህ ያሉንን የአደባባይ በዓላት ካላስፈላጊ የበዓል መወራረስና ድርጊት እንዲቆጠቡ ማድረግ ይገባል ሲል አመላክቷል።

መስቀልን፣ ጥምቀትንና ኢሬቻን ብንመለከት የአገር ውስጥ ምርቶች እንዲያድጉና የእደ ጥበብ ውጤቶች እንዲስፋፉ፣ ባህላዊ ምግቦች፣ እውቀቶችና ሃሳቦች እንዲዳብሩ ያደርጋሉ። በኢትዮጵያ የመስቀል በዓልን አስመልክቶ የሚከበሩ እንደ ጊፋታ፣ ያሆዴና ዮ ማስቀላ የመሳሰሉ በዓላትን ስንመለከት ደግሞ ብዙ ቱሪስት የመሳብና የማቅረብ አቅም ያላቸው በመሆኑ ለገቢ ምንጭነት መጠቀም ያስፈልጋል።

እንደ አቶ ሄኖክ ገለጻ፣ የአደባባይ በዓላቱ ኢትዮጵያን ለማሳየትና ለማስተዋወቅ የተሻሉ የሚባሉ ወቅቶች ላይ የሚከበሩ በመሆኑ የውጭ አገር ጎብኚዎች እነዚን ለመታደም ሲመጡ ጎን ለጎን ተፈጥሮውና ታሪኩን አይተው የሚመለሱበት ዕድልን ይፈጥራሉ። ይህ ደግሞ የጎብኚ ቆይታ በማራዘም በኩል ትልቅ ጉልበት አለው።

በአደባባይ በዓላቱ ብዙ ሕዝብ የሚወጣበትና የማህበረሰቡ እሴትና ባህል በአንድ አውድ የሚታይበት እንዲሁም ብዙ እንግዶች ተመልክተው የሚደሰቱበት ነው። ነገር ግን በዓለም ላይ ካሉ የአደባባይ በዓላት የተሻለ የማስተዋወቅ ሥራ አልተሠራም።

የአደባባይ በዓላቱ የውጭ ምንዛሬ ከማስገኘት ባለፈ በአገር ውስጥ በሚገኙ ግብአቶች የሚመረቱና በእጅ መሥራት የሚችሉ በመሆናቸው ልዩ ያደርጋቸዋል። በዚህም ለአገር ውስጥ ምርቶች እድገት የበኩላቸውን አስተዋጽዖ ያደርጋሉ።

በዓለም ላይ አነስተኛ የሕዝብ ቁጥር የሚሳተፉባቸው የአደባባይ በዓላት በዓለም ትኩረት ተሰጥቷቸው በጉጉት ይጠበቃሉ ያለው ጋዜጠኛ ሄኖክ፣ የኢትዮጵያ የአደባባይ በዓላት በሕዝብ ቁጥር፣ በበዓላቱ አከባበር፣ በኪነ ጥበቡና አከባበራቸው ከቤት የሚጀምሩ በመሆናቸው ዓለም ላይ ከሚከበሩ በዓላት የተሻሉና ድንቅ በመሆናቸው ለኢትዮጵያ የተሻለና የተለየ ዕድል የሚያስገኙ ናቸው ብሏል።

በዓሉን የሚያከብረው ሰው በአለባበሱና በውበት በመጠበቅና የሚታዩ ክፍተቶችን በማስተካከል መቀጠል አለበት። በመንግሥት የአደባባይ በዓላት በሚከበሩበት አካባቢዎች አስፈላጊውን መሠረተ ልማትና ማክበሪያ ቦታዎችን ማመቻቸት ይኖርበታልም ሲልም አመላክቷል።

# ርዕሰ አንቀፅ

## በዓለም አቀፍ ተቋማት ስም በሚፈበረኩና በሚሰራጩ መረጃዎች ላይ ትኩረት ሊደረግ ይገባል !

ትክክለኛ መረጃ የሚመነጨው ከእውነት ነው። እውነት ደግሞ ከሁሉም በላይ ታማኝነትን የሚጠይቅ ከፍ ያለ ሰብዓዊ እሴት ነው። ከዚህ ውጭ ስለመረጃ ሆነ ስለመረጃ ታማኝነት ማውራት የሚቻል አይሆንም። በማውራት ብዛትም ታማኝነትን ለመፍጠር የሚደረግ የትኛውም አይነት ሙከራ ለጊዜው ትርፍ ያስገኘ ቢመስልም ፍጻሜው ግን ተጠያቂነት ማስከተሉ የማይቀር ነው።

በተለይም ከበስተጀርባቸው የፖለቲካ ተልእኮና አጀንዳ ያላቸው "በበሬ ወለደ" ላይ የሚመሰረቱ መረጃዎች የቱንም ያህል በደጋፊና ተሸካሚ የፈጠራ /የውሸት/ ትርክቶች ታጀበው አደባባዮችን የመሙላት አቅም ቢያጎለብቱም "እውነትና ጉም እያደር ይጠራል" እንደሚባለው መጥራታቸው የማይቀር ነው።

መረጃዎች በጠሩ ማግስት የሚፈጥሩት ተጠያቂነት፤ ከፈጠሩት ችግርና ችግሩ ካስከፈለው ዋጋ አንጻር የሚተመን ፤ የታሪክ ተጠያቂነት እስከማስከተል የሚዘልቅ፤ ትውልዶችን እና አገራትን ጭምር አንገት የሚያስደፉ ሊሆን እንደሚችል የተለያዩ አገራትና ሕዝቦች ታሪክ የሚያረጋግጠው እውነታ ነው።

በእኛም አገር ለውጡን ተከትሎ በአገር ውስጥ የሚገኙ የጥፋት ኃይሎች፤ እነሱን መሳሪያ አድርገው የሚጠቀሙ ታሪካዊ ጠላቶቻችንና የለውጡ መንገድ ያላስደሰታቸው ኃይሎች በቅንጅት መረጃዎችን በማፋለስ የለውጡን ኃይል አንገት በማስደፋት ለውጡን ለመቀልበስ የሄዱበት ረጅም ርቀት እንደ ህዝብ ብዙ ዋጋ አስከፍሎናል።

በተለይም አንዳንድ ዓለም አቀፍ ተቋማት በግልጽ ከተቋቋሙበት ዓለም አቀፍ መርህ፤ ከዚያም ባለፈ ከመተዳደሪያ ቻርተራቸው ባፈነገጠ መንገድ ዓለም አቀፍ አሰራርን በሚጻረር ሁንታ የተዛቡ መረጃዎችን በማደራጀትና በማሰራጨት ዓለም አቀፉን ኅብረተሰብ ለማሳሳት በስፋት ሰርተዋል፣ እየሰሩም ነው።

ከለውጡ ማግስት ጀምሮ በሕዝባዊ እንቢተኛነት ከስልጣን የተወገደውን /የአሸባሪውን ትህነግ/ የጥፋት ተግባራት አይቶ እንዳላየ ከመሆን ጀምሮ በቡድኑ የሚፈጠሩ ፈጠራ ትርክቶችን በማስተጋባት በመንግስት ላይ ከፍ ያሉ ጫናዎችን በመፍጠር ለራሳቸው የፖለቲካ ተልእኮ ለማንበርከክ ጥረዋል።

ለዚህም ትልቁን ዓለም አቀፍ ተቋም /የተባበሩት መንግስታት ድርጅትን/ ጨምሮ የአውሮፓ ኅብረት እና ሌሎች ዓለም አቀፍ ተቋማትን ተጠቅመዋል። በተለይም ሰብዓዊ መብቶችን ሽፋን በማድረግ የአገሪቱን ሉዓላዊነት የሚገዳደሩ ተግባራትን ፈጽመዋል። ለዚህም መረጃዎችን ከማዛባት ጀምሮ ፍጹም መሬት ላይ የሌሉ እውነታዎችን ፈጥረው እስከማሰራጨት የደረሰ ድፍረት ውስጥ ገብተው ተስተውለዋል።

እነዚህኑ መረጃዎችን በአንዳንድ ዓለም አቀፍ የመገናኛ ብዙኃን እንዲሰራጩ በማድረግም አገሪቱን እና ሕዝቦቿን ባልተገባ መንገድ ዓለም አቀፍ አጀንዳ ለማድረግ ብዙ ርቀት ሄደዋል። ጫናዎችንና ማዕቀቦችን ለተልእኳቸው ስኬት አቅም መግዣ አድርገው በመጠቀምም የለውጡ መንገድ መንገጫገጭ እንዲበዛበት ሰርተዋል።

መንግስት በሰብዓዊ መብቶችም ሆነ በየትኛውም ጉዳይ ዙሪያ ከየትኛውም አካል ጋር ተባብሮ የመስራት ቁርጠኝነቱን በተደጋጋሚ በየአደባባዮች እያሳወቀ ባለበት እና በተጨባጭም ቁርጠኝነቱን እያሳየ ባለበት ሁኔታ ውስጥ ከመንግስት ጋር ተቀራርቦ ከመስራት ይልቅ መንግስትን ባልተገባ መልኩ በመፈረጅ ለዚሁ የተገዛ መረጃዎችን በመፈብረክና በማሰራጨት ላይ ተጠምደዋል፡፡

ቀደም ባለው ጊዜ የሆነው እንዳለ እንኳን ሆኖ በቅርቡ ራሱን የተመድ የሰብዓዊ መብቶች ኮሚሽን የባለሙያዎች ቡድን በማለት የሚጠራው አካል ይዞት የወጣው ሪፖርት ለዚሁ ተጨማሪ ማሳያ የሚሆን ነው። ገና ከውልደቱ ጀምሮ ሕጋዊነት የሌለው ይህ አካል የተዛባ ድምዳሜውን በተዛባ መረጃ ለማጠናከር የሄደበት ርቀት ቡድኑን ብቻ ሳይሆን ከቡድኑ በስተጀርባ ያለውን ተቋም ተአማኒነት ተጨማሪ ጥያቄ ላይ ጥሎታል።

በአንድ በኩል ለሰብዓዊ መብቶች ተቆርቋሪ ነኝ የሚል ተቋም ከሚያነሳው ጉዳይ ትልቅነት አንጻር፤ ራሱን በሚያሳንሰው መረጃ የመፈብረክ ተግባር ውስጥ መገኘቱ፤ በሌላ በኩል ደግሞ የሚፈበርካቸው መረጃዎች ሰብዓዊ መብቶችን በአደባባይ ለሚጥስ ቡድን /አሸባሪው ትህነግ/ በጥፋት እንዲቀጥልበት የልብ ልብ የሚሰጥ መሆኑ ጉዳዩን አሳሳቢ ያደርገዋል።

ይህ በዓለም አቀፍ ተቋማት ስም የሚደረግ የተዛቡ መረጃዎችን የመፈብረክና እውቅና እንዲያገኙ የሚደረግ የሚዲያ ዘመቻና ጫና፤ የተቋማቱን የቀደመ ስም ከማጉደፍ ባለፈ በነዚህ ተቋማት ላይ እምነት የሚጥሉ አገራትና ሕዝቦችን እምነት በመሸርሸር ቀጣይ ተቋሚዊ ጉዞው ችግር ውስጥ እንዲወድቅ ያደርገዋል።

ከዚያም ባለፈ በተቋሙ ስም የሚፈበረኩ እና የሚሰራጩ የተዛቡና የሚፈበረኩ መረጃዎች አገራትና ሕዝቦችን ሊያስከፍሉ ከሚችሉት ያልተገባ ዋጋ አንጻር የታሪክ ተጠያቂነትን ማስከተላቸው አይቀርም። ከዚህ አንጻር ዓለም አቀፉ ኅብረተሰብ በዓለም አቀፍ ተቋማት ስም በሚፈበረኩና በሚሰራጩ መረጃዎች ላይ በቂ ትኩረት ሊያደርግባቸው ይገባል!

---

ኢፕድ

# አዲስ ዘመን

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስኪያጅ**
ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22

**ዋና አዘጋጅ**
አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**
ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ
ወረዳ 06
የቤት ቁጥር 319
ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et
ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**
ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ
ስልክ፡- 011 126 4240
Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**
- ወርቁ ማሩ
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- አልማዝ አያሌው
- እስማኤል አረቦ

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**
ኢ-ሜይል - etpresspromotion@gmail.com
ስልክ - 011-126-43-41
ፋክስ - 011-811-13-15

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**
ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73
ፋክስ - 011-126-58-12

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**
011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ**
ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70

---

ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው፡፡ በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም፡፡

# ከፍተኛ ትምህርት በኢትዮጵያ እና በዓለም አቀፍ ደረጃ

ጋሹ ሃብቴ (ዶ/ር)

ዶክተር ጋሹ ሃብቴ፣ የመጀመሪያ እና ሁለተኛ ዲግሪያቸውን በአግሪካልቸራል ኢኮኖሚክስ ከሃሮማያ ዩኒቨርሲቲ የያዙ፤ በጅማ እርሻ ኮሌጅ በመምህርነት፣ በትምህርት ክፍል ኃላፊነት፣ በኮሌጅ ዲንነት እና የተማሪዎች ዲን በመሆን አገልግለዋል። በመቀጠልም በኦክለሁማ ስቴት ዩኒቨርሲቲ የዶክተሬት ዲግሪያቸውን በአግሪካልቸራል ኢኮኖሚክስ የሰሩ ሲሆን፤ በአርከንሰስ ስቴት ዩኒቨርሲቲ መምህር ሆነው አገልግለዋል። አሁን ላይ በግል ሥራ ላይ ተሰማርተው ይገኛሉ። በዛሬው የአዲስ ዘመን የነጻ ሃሳብ አምድም የከፍተኛ ትምህርት ጥቅምን መሰረት በማድረግ በዓለም አገራት ያለበትን ደረጃ በማመላከት በኢትዮጵያ ያለውን ሁነት በሚከተለው መልኩ ለአንባብያን ይድረስልኝ ብለው አቅርበዋል።

ከፍተኛ ትምህርት በማንኛውም አገር ዜጎች የሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸውን ከጨረሱ በኋላ በተለያየ ደረጃ የሚከታተሉት የትምህርት ደረጃ ነው። ከፍተኛ ትምህርት አገልግሎት በተለያዩ አገራት በተለያየ አቀራረብ ለዜጎች የሚሰጥ አገልግሎት ነው። ይህ የተለያየ የከፍተኛ ትምህርት አሰጣጥ አገልግሎት በተለያዩ አገራት የተለያየና እጅግ በጣም የተራራቀ ደረጃ አለው። በዘርፉም የሚሰጠው አገልግሎት የተለያየ በመሆን ለህብረተሰብ የሚሰጠው የጥቅምና ለውጥም እንደተሰጠው የትምህርት ደረጃ እና አገልግሎት ይለያያል።

የዚህ ጽሁፍ ዋና አላማው በዚህ ረገድ አገራችን የት ነው ያለችው የሚለውን ለመዳሰስ ሲሆን፤ ለፖሊሲ አውጭዎችም የከፍተኛ ትምህርትንም አስፈላጊነት በተመለከተ አቅጣጫ ይሰጣል የሚል ግምት ስላለኝ ነው። አሁን ስላለው የተለያዩ ደረጃ ጠለቅ ብለን ከማየታችን በፊት ለመሆኑ የከፍተኛ ትምህርት በአጠቃላይ ሲታይ የሚሰጣቸው ዋና ዋና አገልግሎቶች ምንድን ናቸው? የሚለውን ማየቱ እጅግ በጣም አስፈላጊ ይሆናል። በዚህ ረገድ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ዋነኛ ስራቸው መሆንና ማካተት ያለባቸው የሚከተሉትን 5 ዋና ዋና አገልግሎቶችን ነው።

1ኛ. የከፍተኛ ትምህርት ተቋሞች በዋነኝነት የሚታወቁበትና የሚታየው የማስተማር አገልግሎት ነው። በርካታ ተቋማት ይህን የማስተማር አገልግሎት በመስጠትና ዜጎችን በተለያየ የሙያ ዘርፎች በማሰልጠን ለአገርና ለእራሳቸው የሚውል አገልግሎቶች ይሰጣሉ። በዚህ ረገድ በዓለም ዙሪያ ያሉ አገሮች ለዜጎቻቸው የሚሰጡት የማስተማር አገልግሎት የተለያየ ደረጃ ያለው ሲሆን፤ ይህን እንደየአገሮቹ አቅም፣ ጥረቶችና ለትምህርት እንደሚሰጡት ዋጋ ይለያያል። በየአገሩ ያለው የተማረ ሰው ቁጥር መለያየት በተለያየ ምክንያት ቢሆንም ዋነኛዎቹ ግን የመንግስትና የአገር አቅም፣ ጥረትና ትኩረት ዋነኛውን ሚና ይጫወታሉ።

2ኛ. የአብዛኛው ወይም የብዙዎች የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ትኩረትና አገልግሎት የጥናትና ምርምር ስራ ነው። በዓለም ዙሪያ ባሉ አገሮች ሁሉ እጅግ የተማረ ሰው በብዛት ከሚታይባቸው ተቋሞች ውስጥ የከፍተኛ ትምህርት አንዱና ከፍተኛውን ቦታ የያዘ እንደሚሆን ምንም አያጠራጥርም። በግል ችሎታቸውም ሆነ በአመችነቱ የከፍተኛ ትምህርት መምህራን ከብሔረሰብ ተኮር እስከ አገራዊ እና አለማቀፋዊ በሆኑ ጉዳዮች በመመራመር አዲስ ግኝቶችንና ላለ ችግር መፍትሄ የሚሆኑ አገልግሎቶችን በመስጠት ይታወቃሉ። ስለሆነም ይህ አቅም፤ የአመራርና የአላማ ልዩነት ካልሆነ በስተቀር ሌላው ዋናው የከፍተኛ ትምህርት ቤቶች ኃላፊነት ነው። በዚህ ረገድ በከፍተኛ ትምህርት መምህራን የተገኙ የጥናት ውጤቶች ለዓለም ህብረተሰብ በተለያየ ዘርፍ እድገት እጅግ በጣም ከፍተኛ እንደሆነ ይታወቃል።

3ኛ. የከፍተኛ ትምህርት ቤቶች ኃላፊነትና የስራ ድርሻ ለአካባቢ እድገት አገልግሎት መስጠት ነው። (outreach program) ይህ በአብዛኛው ጎልቶ የሚታየው በእርሻ፤ በጤና፤ በትምህርት፤ በከተማ ልማትና በሌሎች አገልግሎቶች የሚሰለጥኑ ተማሪዎችና መምህራን የሚሰጡት አገልግሎት ነው። በአደጉ አገሮች ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት በዚህ አገልግሎት ዘርፍ እጅግ በጣም ሰፊና ከፍተኛ ውጤት ያስገኙ አገልግሎቶችን ይሰጣሉ። በአገራችንም የሐሮማያ ዩኒቨርሲቲ፤ የጅማ የእርሻ ኮሌጅና በሌሎችም ተቋሞች፤ በዚህ ረገድ ጠንካራ ፕሮግራም እንደነበራቸው ይታወቃል። መምህራን ከማስተማርና ከመመራመር ስራቸው በተጨማሪ በዋነኝነት የከፍተኛ ትምህርት ቤት ባሉባቸው አካባቢዎች የሚያከናውኑት ኃላፊነት ነው። በማስተማር የበለጸገ እውቀትንና በምርምር የሰላ ችሎታን በተግባር ላይ በማዋል ለአካባቢ ህብረተሰብ አገልግሎት የመስጠት ኃላፊነት እና ስራ በተለይ በሰለጠኑት አገሮች እጅግ በጣም ከፍተኛ ውጤትና ጥቅም ያስገኘ የከፍተኛ ትምህርት ተቋሞች የአገልግሎት ዘርፍ ነው።

4ኛ. የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የስራ ድርሻ ችሎታው ኑሯቸው መማር ወይም መሳተፍ ላልቻሉና የተወሰነ ደረጃ ተምረው የሚቀጥለውን የትምህርት ደረጃ መማር ለሚፈልጉ የተለያዩ ትምህርትን (continuing education or extinction education) የመስጠት ኃላፊነት ነው። በዚህ ረገድ የከፍተኛ ትምህርት ተቋሞች በርካታ ዜጎች በመደበኛ ትምህርት ለመማር ያላገኙትን እድልና ተሳትፎ እንዲያገኙ የሚያደርጉበት አገልግሎት ነው። በተለያየ ምክንያት ችሎታው ሳያንሳቸው መማር ላልቻሉ አገልግሎት የመስጠትና በሚሳተፉበት ስራ ምርታማ እንዲሆኑ ለዜጎች የሚሰጥ አገልግሎት ነው። በዚህ ረገድ አንዳንድ አገሮች እጅግ አድርገው ለዜጎቻቸው ከፍተኛ ትምህርት እንዲዳረስ አድርገዋል። ታዳጊ አገሮች ግን ብዙም ትኩረት ያልሰጡት የከፍተኛ ትምህርት አገልግሎት እንደሆነ ይታወቃል። በዚህ አገልግሎት ተምረው ከፍተኛ ደረጃ የደረሱና ጥሩ አገልግሎት የሚሰጡ ዜጎች መኖራቸው የሚታወቅ ቢሆንም ይህ ዘርፍ በህብረተሰቡ ብዙ የማይታወቅና የሚወራለት የከፍተኛ ትምህርት ቤቶች አገልግሎት አይደለም።

በ1988 ዓ.ም የኢትዮጵያ ከፍተኛ ትምህርት ኮሚሽን የከፍተኛ ትምህርት በተለያዩ አህጉራት ምን እንደሚመስል የሚያጠና በርካታ ቡድን ልኮ ነበር። በመካከለኛው ምስራቅ አገራት ከፍተኛ ትምህርት ምን እንደሚመስል የሚያጠኑ ሁለት አንጋፋ የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ መምህራን ሪፖርትን እንደማስታውሰው፣ በጠቅላላው በኢትዮጵያ ያሉ 3 ዩኒቨርሲቲ እና 6 ኮሌጆች (አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ ሐሮማያ ዩኒቨርሲቲ፣ አስመራ ዩኒቨርሲቲ፣ ጅማ እርሻ ኮሌጅ፣ አምቦ እርሻ ኮሌጅ፣ የንግድ ስራ ትምህርት ቤት፣ የኮተቤ ኮሌጅ፣ የፖሊ ቴክኒክ ትምህርት ቤትና የናዝሬት ቴክኒካል ትምህርት ቤት) ውስጥ የነበሩ ተማሪዎች ቁጥር 18,000 ገደማ ሲሆኑ በግብጽ በካይሮ ዩኒቨርሲቲ ብቻ የተከታታይ ትምህርት ተማሪዎች ቁጥር 12,000 እንደነበረ ሪፖርት መደረጉ አስታውሳለሁ። ስለዚህ አገሮች በዚህ አገልግሎት ትኩረት በመስጠት ለዜጎቻቸው ከፍተኛ ትምህርት አገልግሎትን በማዳረስ የዜጎችን ምርታማነትና የስራ እድል መለወጥ እንደሚቻል መጤን አለበት።

5ኛ. የከፍተኛ ትምህርት ተቋሞች በየአካባቢው በተለያየ ደረጃ የስራ እድልን በመክፈት በርካታ የአካባቢ ነዋሪዎች የስራ እድል እንዲያገኙ በማድረግ ይረዳሉ። በተጨማሪም ዘመናዊ አኗኗርን (ትምህርት፤የጤና፣ ቤተሰብ አያያዝንና በርካታ አገልግሎቶችን) ያሳድጋል።

በዚህ አገልግሎት ዘርፍና ሌሎችም ካሉ ይህን ጉዳይ ለምን ማንሳት አስፈለገ ለሚሉ ከወዲሁ መልሱ ከፍተኛ ትምህርት መስፋፋትና መብዛት ለአገር እድገትና ለዜጎች የተሻለ ሕይወት መኖር በርካታ አገልግሎቶችና ጥቅም ስላለው ነው። ዘርዘር ባለ መልኩ ሊጠቃለሉ ከሚችሉ የከፍተኛ የትምህርት ጥቅሞች መካከል፡-

- የተማረ ዜጋ ለአገሩና ለሌሎች የሚተርፍ የመፍጠር ችሎታ (critical thinking and innovative personality) ሊኖረው ይችላል። ይህም የፈጠራ ስራ እያደገና እየሰፋ ሲሄድ የአካባቢ፤ አገራዊና አላማ አለማቀፋዊ ቅርጽ ሊይዝ ይችላል። ይህንን ስናነሳ ሊታወሰን የሚገባው አውሮፕላን ስለፈጠሩ ሰዎች፣ ስልክን ስለፈጠሩ ሰዎች፣ መኪናን ስለፈጠሩ ሰዎች፣ ኮምፒውተርን ስለፈጠሩ ሰዎች፣ መድኃኒትን ስለፈጠሩ ሰዎች እና ስለሚፈጥሩ ማሰቡ ብቻ የከፍተኛ ትምህርትንና የፈጠራን ስራ አንድ ላይ ለማየት ያስችላል።
- ከፍተኛ ትምህርት አገልግሎቶች ዜጎች የተደላደለ የንብረት ባለቤት እንዲሆኑ ያደርጋቸዋል። ይህም ማለት ትምህርት ድህነትን ይቀንሳል አማካኝ ገቢንም ይጨምራል። በአጠቃላይ የተማረ ዜጋ በአማካኝ ገቢው ከፍ ያለ ነው። ስለዚህ የሌሎች ዜጎች ሕይወትን የመጥቀም አስተዋጽኦ አለው።
- የከፍተኛ ትምህርት ዜጎችን በተለያዩ ዘርፍ የበለጠ ምርታማ እንዲሆኑ ያደርጋል፤ ይረዳል።
- ከፍተኛ ትምህርት አገልግሎት ስነስርዓት እና ህግ አክባሪነትን ያሳድጋል በአንዳንድ ከፍተኛ የተማረ የሰው ኃይል ባላቸው የዓለም አገሮች በውትድርናና፣ በጥበቃ የሚያገለግል ዜጋ በጣም አነስተኛ ነው።
- የከፍተኛ ትምህርት በዜጎች መካከል ያለውን የእኩልነት ሀሳብ ያሳድጋል በተለይ የጾታ እኩልነትን ከፍ ያደርጋል።
- የከፍተኛ ትምህርት ለህብረተሰብ ጎጂ የሆኑ ባህሎችን በማሻሻል ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያደርጋል ለምሳሌ ያህል ያለእድሜ ጋብቻ ልማድን ይቀንሳል።
- የተማረ ህብረተሰብ በአካባቢ የአየር ለውጥ ደህንነት(environmental changes development) ላይ አውንታዊ አስተዋጽኦ ማድረግ ይችላል።
- የከፍተኛ ትምህርት ዜጎች ዘመናዊና በማንኛውም መልኩ ጤናማ ኑሮ (Modern society that is willing to use science) እንዲኖር ይረዳል።
- የከፍተኛ ትምህርት በራስ መተማመንንና እራስ መቻልን ያሳድጋል (develop confidence and independence)፤ እጅግም አድርጎ ያጠናክረዋል፤
- ከፍተኛ ትምህርትን መማር የመረጃን ከቦታ ወደ ቦታና በአገሮችም መካከል እንዲዘዋወርና እንዲተላለፍ አቅም ያሳድጋል (carey and transfer use full information and knowledge )
- ከፍተኛ ትምህርት አገልግሎት ከሌሎች ባህሪይ የአሰራር ልምድና ባህል ተምሮ ለራስና ለሌሎች ለማስተላለፍ እንዲቻል ይጠቅማል።
- ከፍተኛ ትምህርት መማር በተለያየ መልክ ያሉ ችግሮችን የመቅረፍ ችሎታን ያሳድጋል ( problem solving skill)

ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የተማሩ ዜጎች በአጠቃላይ ከላይ የተጠቀሱትንና ሌሎችንም ለማህበረሰብ ከፍተኛ ጥቅም የሚሰጡ አገልግሎቶችን ይሰጣሉ። በአገሮች መካከል ያለ የሀብትና የአኗኗር ልዩነት በአብዛኛው በተማሩ ዜጎች መጠን፤ ጥራትና አገልግሎት ላይ የተመሰረተ ነው።

የከፍተኛ ትምህርት አገልግሎት ከላይ የተጠቀሱትንና ሌሎችም በርካታ ጥቅሞች ለዜጎች ይሰጣል። ይህን ካልን ለመረጃነት ዜጎቻቸውን በከፍተኛ ደረጃ ያስተማሩ ጥቂት አገራትን ከላይ ከጠቀስኩት ጥቅሞች ጋር በማጣጣም በመረጃነት የሚከተሉትን ሰንጠረዦች መመርመር እንችላለን።

ወደ ገጽ 6 ዞሯል

**ነፃ ሃሳብ**

# ከፍተኛ ትምህርት በኢትዮጵያ ...

ከገጽ 5 የዞረ

**ሰንጠረዥ 1** ዩኒቨርሲቲዎች በዓለም ካሉ 15 ብዙ ህዝብ ባላቸው አገሮች፤

| ተ.ቁ | አገር | ህዝብ ሚሊየን | የኒቨርሲቲ ቁጥር | የኒቨርሲቲ ቁጥር በ10 ሚሊየን | የሐኪም ቁጥር በ1000 |
|---|---|---|---|---|---|
| 1 | ቻይና | 1.4 ቢሊየን | 2565 | 19.3 | 2.0 |
| 2 | ህንድ | 1.3 ቢሊየን | 5288 | 40.6 | 0.9 |
| 3 | አሜሪካ | 330 | 3266 | 97.4 | 2.6 |
| 4 | ኢንዶንዢያ | 273 | 2595 | 95.0 | 0.5 |
| 5 | ፓኪስታ | 220 | 385 | 17.5 | 1.1 |
| 6 | ብራዚል | 212 | 1297 | 61.5 | 2.3 |
| 7 | ናይጄሪያ | 206 | 279 | 14.8 | 0.8 |
| 8 | ባንግላዲሽ | 164 | 170 | 10.6 | 0.6 |
| 9 | ራሺያ | 145 | 1053 | 75.2 | 4.4 |
| 10 | ሜክስኮ | 128 | 1173 | 97.2 | 4.8 |
| 11 | ጃፓን | 126 | 1063 | 84.3 | 2.5 |
| 12 | ኢትዮጵያ | 114 | 70 | 6.6 | 0.1 |
| 13 | ፍሊፒንስ | 109 | 290 | 26 | 0.6 |
| 14 | ግብጽ | 104 | 73 | 7.3 | 0.8 |
| 15 | ቬትንሀም | 93 | 180 | 18.5 | 0.8 |

በዚህ ሰንጠረዥ አገራችን በህዝብ ቁጥር 12ኛ ስትሆን በዩኒቨርሲቲ ቁጥርም ሆነ በጤና ሚዛን የመጨረሻ ደረጃ ላይ ስትሆን፤ ለዚህ በምንጭነት የተጠቀምኩትም worldometer.com እና index mund ናቸው፡፡

በተመሳሳይ መልኩ በዓለም ዙሪያ ካሉ ብዙ ህዝብ ካላቸው አገሮች በተጨማሪ በአፍሪካ ያሉ 15 ብዙ ህዝብ ያላቸውን አገሮች የከፍተኛ ትምህርት ተቋም የሚከተለውን ይመስላል፡፡

**ሰንጠረዥ 2** የ15 የአፍሪካ አገሮች የዩኒቨርሲቲዎች ብዛት (2020) ማሳያ፤

| ተ.ቁ | የአፍሪካ አገሮች | የሕዝብ ብዛት | ዩኒቨርሲቲ | ዩኒቨርሲቲ 10 ሚሊየን | ሐኪሞች 1000 |
|---|---|---|---|---|---|
| 1 | ናይጄሪያ | 206 | 226 | 14.8 | 0.04 |
| 2 | ኢትዮጵያ | 114 | 70 | 6.6 | 0.10 |
| 3 | ግብጽ | 101 | 73 | 7.3 | 0.79 |
| 4 | ዲሞክራቲክ ኮንጎ | 89 | 40 | 4.4 | 0.11 |
| 5 | ደቡብ አፍሪካ | 59 | 104 | 17.6 | 0.91 |
| 6 | ታንዛኒያ | 59 | 52 | 8.6 | 0. 10 |
| 7 | ኬኒያ | 53 | 129 | 24.3 | 0.02 |
| 8 | ዩጋንዳ | 45 | 69 | 13.3 | 0.02 |
| 9 | አልጄሪያ | 43 | 104 | 24.1 | 1.83 |
| 10 | ሱዳን | 43 | 58 | 13.4 | 0.41 |
| 11 | ሞሮኮ | 36 | 25 | 6.4? | 0.73 |
| 12 | አንጎላ | 32 | 23 | 7.1 | 0.21 |
| 13 | ጋና | 31 | 70 | 22.5 | 0.18 |
| 14 | ሞዛምቢክ | 27 | 16 | 5.9 | 0.07 |
| 15 | ማዳገስካር | 27 | 12 | 4.4 | 0.18 |

**ሰንጠረዥ 3** የህዝብ ብዛት ደረጃን ተከትሎ የ15 የአፍሪካ አገሮች በ10 ሚሊዮን ህዝብ ያላቸው የዩኒቨርሲቲ ቁጥር በደረጃ፤

| ተ.ቁ | አገር | ዩኒቨርሲቲ ለ10 ሚሊየን ህዝብ |
|---|---|---|
| 1 | ኬኒያ | 24.3 |
| 2 | አልጄሪያ | 24.1 |
| 3 | ጋና | 22.5 |
| 4 | ደቡብ አፍሪካ | 17.6 |
| 5 | ናይጄሪያ | 14.8 |
| 6 | ሱዳን | 13.4 |
| 7 | ኡጋንዳ | 13.3 |
| 8 | ታንዛኒያ | 8.8 |
| 9 | ግብጽ | 7.3 |
| 10 | አንጎላ | 7.1 |
| 11 | ሞሮኮ | 7.1 |
| 12 | ኢትዮጵያ | 6.6 |
| 13 | ሞዛንቢክ | 6.6 |
| 14 | ዲሞክራቲክ ኮንጎ | 5.9 |
| 15 | ማዳካስካር | 4.4 |

**ሰንጠረዥ 4** በዓለም ደረጃ ለ10 ሚሊየን ህዝብ አገሮች ያላቸው የዩኒቨርሲቲ ቁጥር በደረጃ፤

| ተ.ቁ | አገር | የህዝብ ብዛት በሚሊየን | ዩኒቨርሲቲዎች በቁጥር | የዩኒቨርሲቲ በ10 ሚሊየን | |
|---|---|---|---|---|---|
| 1 | ማሌዢያ | 32 | 374 | 116 | እነዚህ 18 አገሮች አሁን ያሉበት የእድገት ደረጃ ከመድረሳቸው በፊት በአንድ ወቅት አሁን ኢትዮጵያ ያለችበትን የእድገት ደረጃ አልፈው ነው፡፡ ለእድገታቸው ዋነኛና መሰረታዊ ከሆኑት ምክንያቶች ዋናዎቹ የአስተዳደር በጎነትና፤ የተፈጥሮ ሀብት ሲሆን ከዚህ በተጨማሪ ዜጎቻቸውን እጅግ በጣም በከፍተኛ ደረጃ በማስተማራቸው ነው፡፡ |
| 2 | ካናዳ | 38 | 386 | 101 | |
| 3 | ፖላንድ | 38 | 377 | 99 | |
| 4 | አሜሪካ | 330 | 3216 | 97 | |
| 5 | ሜክሲኮ | 128 | 1173 | 97 | |
| 6 | ኢንዶኔዢያ | 273 | 2595 | 95 | |
| 7 | ፈረንሳይ | 83 | 617 | 94 | |
| 8 | ጃፓን | 126 | 1063 | 84 | |
| 9 | ኢራን | 83 | 703 | 84 | |
| 10 | ዩክሬን | 44 | 315 | 81 | |
| 11 | ራሺያ | 145 | 1053 | 75 | |
| 12 | ደቡብ ኮሪያ | 52 | 375 | 72 | |
| 13 | ብራዚል | 212 | 1297 | 61 | |
| 14 | ጀርመን | 83 | 459 | 55 | |
| 15 | ስፔን | 48 | 266 | 55 | |
| 16 | ኮሎምቢያ | 51 | 293 | 57 | |
| 17 | ዩናይትድ ኪንደም | 67 | 280 | 41 | |
| 18 | ህንድ | 1.38 ቢሊዮን | 5288 | 40 | |

| ደረጃ | አገር | ሕዝብ በሚሊየን | ዩኒቨርሲቲ (ቁጥር) | ዩኒቨርሲቲ በ10ሚሊየን |
|---|---|---|---|---|
| 24 | ኬንያ | 53 | 129 | 24.3 |
| 25 | አልጄሪያ | 43 | 104 | 24.1 |
| 26 | ጋና | 31 | 70 | 22.5 |
| 27 | ደቡብ አፍሪካ | 59 | 121 | 20.5 |
| 28 | ኢትዮጵያ | 114 | 70 | 6.6 |

**ሰንጠረዥ 5** በዓለም ያሉ አገራት የዩኒቨርሲቲዎቻቸው ቁጥር እና የሕዝብ ብዛት ንጽጽር፤

| ደረጃ | አገር | ዩኒቨርሲቲ | ህዝብ ብዛት (ሚሊየን) | ደረጃ | አገር | ዩኒቨርሲቲ | ህዝብ ብዛት |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | ህንድ | 5288 | 1.3(ቢሊየን) | 28 | ቬትናም | 180 | 93 |
| 2 | አሜሪካ | 3216 | 330 | 29 | ባንግላድሽ | 170 | 164 |
| 3 | ኢንዶኔሽያ | 2595 | 273 | 30 | ታይዋን | 165 | 23 |
| 4 | ቻይና | 2565 | 1.4(ቢሊየን) | 31 | ሞሮኮ | 148 | 36 |
| 5 | ብራዚል | 1297 | 212 | 32 | አርጄንቲና | 145 | 45 |
| 6 | ሜክሲኮ | 1173 | 128 | 33 | ካዛክስታን | 134 | 19 |
| 7 | ራሽያ | 1058 | 141 | 34 | ፔሩ | 133 | 32 |
| 8 | ጃፓን | 1008 | 126 | 35 | ቺሌ | 131 | 19 |
| 9 | ኢራን | 704 | 83 | 36 | ኔዘርላንድ | 129 | 17 |
| 10 | ፈረንሳይ | 617 | 65 | 37 | ኬንያ | 123 | 53 |
| 11 | ጀርመን | 459 | 83 | 38 | ኢራቅ | 115 | 40 |
| 12 | ካናዳ | 387 | 38 | 39 | ፖርቹጋል | 109 | 10 |
| 13 | ፖላንድ | 379 | 38 | 40 | ደቡብ አፍሪካ | 104 | 59 |
| 14 | ደብብ ኮሪያ | 375 | 56 | 41 | ስዊዘርላንድ | 102 | 8.6 |
| 15 | ማሌዥያ | 374 | 32 | 42 | አልጄሪያ | 102 | 43 |
| 16 | ፓኪስታን | 358 | 220 | 43 | ሮማንያ | 99 | 19 |
| 17 | ዩክሬን | 315 | 43 | 44 | አፍጋንስታን | 95 | 38 |
| 18 | ኮሎምቢያ | 293 | 51 | 45 | ማይናማር | 89 | 54 |
| 19 | ፊሊፒን | 290 | 67 | 46 | ኦስትርያ | 85 | 9 |
| 20 | እንግሊዝ | 280 | 67 | 47 | ኡዜብኪስታን | 83 | 33 |
| 21 | ናይጄሪያ | 279 | 206 | 48 | ሶማሊያ | 83 | 16 |
| 22 | እስፔን | 266 | 48 | 49 | ቤልጅየም | 81 | 11.6 |
| 23 | ጣሊያን | 239 | 60 | 50 | ዴንማርክ | 73 | 5.8 |
| 24 | ቱርክ | 213 | 84 | 51 | ግብጽ | 73 | 104 |
| 25 | ቱኒዚያ | 203 | 12 | 52 | ስስቼዝያ | 70 | 10 |
| 26 | ታይላንድ | 194 | 69 | 52 | ሀንገሪ | 70 | 9.6 |
| 27 | አውስትራሊያ | 190 | 26 | 52 | ሰርቢያ | 70 | 8.6 |
| | | | | 52 | ኢትዮጵያ | 70 | 114 |

ከዚህ እንደምንረዳው ኢትዮጵያ በዓለም በህዝብ ብዛቷ 12ኛ ነች በቆዳ ስፋቷ ደግሞ 27ኛ ነች፡፡ በዓለም ካሉት 30 ሚሊዮን ህዝብ ካላቸው አገሮች ጋር ሲነጻጸር በዩኒቨርሲቲ ቁጥር 33ኛ ነች፡፡ በአጠቃላይ በዓለም ካሉት አገሮች ጋር ስትነጻጸር ግን 52ኛ ነች፡፡ ስለዚህ የመማር፤ የምርምር፣ የተከታታይ ትምህርት፤ የአካባቢ አገልግሎትና የስራ እድል የሚሰጡ ዩኒቨርሲቲዎችን ቁጥር ማሳደግ ያስፈልጋታል፡፡ በአፍሪካ ኢትዮጵያ በህዝብ ብዛት 2ኛ ስትሆን ባላት ዩኒቨርሲቲ ቁጥር 7ኛ ነች፡፡ የሐኪም ብዛት በ1000 ህዝብ 0.10 ሐኪም በመሆን ከሌሎች የአፍሪካ አገሮች ጋር ሲወዳደሩ በጣም ዝቅተኛ ነው፡፡ ይህም የከፍተኛ ትምህርትን መስፋፋት አስፈላጊነትን ያሳያል፡፡ ይሄም በአለን የዩኒቨርሲቲ ቁጥር ከአመታት በፊት ከነበረው በመጨመሩ ተኩራርተን የዩኒቨርሲቲ ግንባታና ቁጥር መጨመርን በምንም መልኩ ወደኋላ ማለት እንደሌለብን ፖሊሲ አውጭዎቹ ማጤን እንዳለባቸው ያስገነዝበናል፡፡

ለዚህ ጽሁፍ ያነሳሳኝን ዋነኛው ጉዳይ ጥራትን እንደ ምክንያትና ችግር በማንሳት ዩኒቨርሲቲ አለመገንባትና አለመጨመርን እንደመፍትሄ በመቁጠር በርካታ ባለስልጣናትና እና ምሁራን በተደጋጋሚ ሲናገሩ በመስማቴ ነው ከላይ እንደ ጠቀስኩት የትምህርት ተቋማት ኃላፊነትና የስራ ድርሻ ከማስተማር በተጨማሪ የምርምሩን፤ የአካባቢ አገልግሎት፤ የተከታታይ ትምህርትንና የስራ እድልን የመስጠት አገልግሎታቸውን በፍጹም ወደኋላ መባል የሌላባቸው አስተዋጽኦዎች እንደሆኑ በሚገባ ማስተዋል እንዳለብን ለማሳሳብ እወዳለሁ፡፡

ኢኮኖሚ

# ሳይንስና ቴክኖሎጂ

## የተገልጋዮችንና የደንበኞችን አስተያየት በቴክኖሎጂ የማቅረብ ጅምር

**አንተነህ ቸሬ**

ተቋማት የተገልጋዮቻቸውንና የደንበኞቻቸውን እርካታ ለማወቅ ከሚጠቀሙባቸው የአሰራር ዘዴዎች መካከል የሃሳብ መስጫ ሳጥኖችና መዝገቦች ተጠቃሽ ናቸው።እነዚህ የሃሳብ መስጫ ሳጥኖችና መዝገቦች ደንበኞችና ተገልጋዮች በተቋማት ውስጥ ስለታዘቡት አሰራር ሃሳባቸውን የሚገልፁባቸው የአስተያየት መግለጫዎች እንደሆኑ ይታመናል።

ይሁን እንጂ እነዚህ ዘዴዎች ብዙ ጉድለቶች አሉባቸው።ተገልጋዮችና ደንበኞች ሃሳባቸውን በጽሑፍ ለማስፈር ከሚያሳዩት ተነሳሽነት ጀምሮ፤ አስተያየቶች የተሰጧቸው ተቋማት የተገልጋዮችን ሃሳብ በትኩረት ለመመልከት እስከሚኖራቸው ትጋት ድረስ ብዙ ጥያቄዎች ይነሱባቸዋል።በሌላ በኩል የተገልጋዮች ሃሳቦች/አስተያየቶች የተቋማትን አሰራር ለማሻሻል ቀላል የማይባል ፋይዳ አላቸው።ስለሆነም የተገልጋዮችንና የደንበኞችን ሃሳቦችና አስተያየቶች ቀላል፣ ግልጽና አስተማማኝ በሆነ መልኩ ተቀብሎ የአገልግሎት አሰጣጥን በማሻሻል ተመራጭና ውጤታማ ተቋም ለመሆን ይህን እውን ማድረግ የሚያስችል አሰራር ያስፈልጋል።

ታምሩ ካሣ የማኅበረሰቡን ችግሮች የሚያቃልሉ የፈጠራ ስራዎችን የሚሰራ የፈጠራ ባለሙያ ነው።ከፈጠራ ስራዎቹ መካከልም ወረቀት አልባ የተገልጋዮች የቅሬታ መቀበያና መልስ መላኪያ ቴክኖሎጂ ይጠቀሳል።በ2001 ዓ.ም መጨረሻ አንድ ማየት የተሳነው ግለሰብ ወደ አንድ መስሪያ ቤት ሄዶ መስሪያ ቤቱ ባስቀመጠው የአስተያየት መስጫ መዝገብ ላይ አስተያየቱን ለመፃፍ ሲቸገር ይመለከታል።በወቅቱም ታምሩ ግለሰቡ ሃሳቡን እንዲነግረውና እርሱ እንደሚፅፍለት ነገረው።ይሁን እንጂ ታምሩ ለግለሰቡ በዚህ መልኩ ትብብር ቢያደርግለትም፣ እንደዚህ ግለሰብ መፃፍ የማይችሉ ሌሎች በርካታ ግለሰቦች መኖራቸውን ሲያስብ ‹‹እነርሱስ?›› ከሚል ትልቅ ጥያቄ ጋር ተፋጠጠ።በየመስሪያ ቤቱ ያለው የአገልግሎት አሰጣጥ ችግር ብዛት እና ተለምዷዊውና ወረቀትን መሰረት ያደረገው የሃሳብ አሰጣጥ ዘዴ ያሉበት ጉድለቶችም ተጨማሪ ጥያቄ ሆነው መጡ።ታምሩም ለነዚህ ጥያቄዎች አስተማማኝ ምላሽ የሚሰጥ መፍትሄ ለመፈለግ ተነሳ።

የመጀመሪያውና ቀለል ያለው አማራጭ ድምጽን በካሴት በመቅረፅ አስተያየትን ማስቀመጥ የሚያስችል ሁኔታን ፈጠረ።ይህም አሰራር ብዙ ጉድለቶች ያሉበት ሆኑበት፤ ከዚያም ፈጠራው አስተያየትን በዲጂታል መቅረፀ ድምፅ (Digital Voice Recorder) ወደ ማቅረብ ተሸጋገረ።ይህኛውም ዘዴ በቂ ባለመሆኑ ወደተሻለ የአሰራር ስርዓት መሸጋገር አስፈላጊ ሆነ።ይህ የተሻለ የአሰራር ዘዴ ፍለጋም የታምሩን የፈጠራ ስራ አሁን ወዳለበት ደረጃ አሳደገው።

በ2002 ዓ.ም የተጀመረው የታምሩ የፈጠራ ስራ በ2008 ዓ.ም ወደ ተቋም ገብቶ አገልግሎት መስጠት ጀመረ።በወቅቱ ታምሩ የፈጠራ ስራውን ኤግዚቢሽን ላይ አቅርቦት ስለነበር ስራውን የተመለከተው የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኮሚሽን የታምሩን የፈጠራ ውጤት ስራ ላይ አዋለው።‹‹ታምቴክ ሶሉሽንስ›› የተሰኘውን የፈጠራ ስራዎቹን የሚያቀርብበትን ድርጅት የመሰረተውም በዚሁ ወቅት ነበር።በመቀጠልም የፈጠራ ስራው ልዩ ልዩ ማሻሻያዎች ተደርገውበት ከአንድ ዓመት በፊት፣ በ2014 ዓ.ም፣ አሁን ያለውን ቅርፅና ደረጃ ያዘ።

ታምሩ እንደሚያስረዳው፣ በሶፍትዌር የታገዘው ይህ ቴክኖሎጂ፣ የተገልጋዮችን ሃሳብና አስተያየት ባህረ መዝገብ ላይ ማስፈር ተለምዷዊ አሰራር የቀየረ ነው።በተለምዷዊው የሃሳብና አስተያየት አሰጣጥ ዘዴ ሰዎች ሃሳባቸው ለሚመለከተው የሥራ ክፍል ይደርስልናል የሚል እምነት የላቸውም።የሰጡት ሃሳብና አስተያየት ተቀድዶ ሊጣልም ይችላል።

ወረቀት አልባው የተገልጋዮች የቅሬታ መቀበያና መልስ መላኪያ ቴክኖሎጂ 10 ነጥብ አንድ ኢንች ስፋት ባለው ስክሪን ላይ የሚሰራ ሲሆን፤ ሴንሰር (Sensor)፣ የኦፕሬተር ድምፅ እና የድምጽ መቀበያ አምፕሊፋየር አሉት።በዚህ ቴክኖሎጂ ላይ የሰርቨር ተከላም ሆነ የኬብል ዝርጋታ አያስፈልጉም።

ሰዎች ቦታው ላይ ሲደርሱ ማሽኑ ላይ የተገጠመው ሴንሰር ‹‹ ... እባክዎ አስተያየትዎን ይስጡ ...›› የሚል የድምጽ ግብዣ ከማሽኑ እንዲቀርብላቸው ያደርጋል።ተገልጋዮችም ከማሽኑ በሚሰጣቸው መመሪያ መሰረት ሃሳባቸውን ይናገራሉ።ማሽኑ ሃሳብ ለመቀበል ያስቀመጠው የጊዜ ገደብ አለ።ተገልጋዮች በተፈቀደላቸው የጊዜ ገደብ ሃሳባቸውን ካልጨረሱ ተጨማሪ ሰዓት ስለሚሰጣቸው በማሽኑ የታዘዘውን ቦታ በጣት በመጫን ቀሪውን ሃሳባቸውን መናገር ይችላሉ።ማሽኑም አስተያየቶቹን በመያዝ (በመቅዳት) ወደሚመለከተው አካል እንዲደርሱ ያደርጋል።




**ቴክኖሎጂው ቦታ የማይፈጅ፣ ብዙ መሰረተ ልማቶችን የማይጠይቅ፣ በቀላሉ መንቀሳቀስ የሚችልና ለአጠቃቀምም ቀላል በመሆኑ ተቋማት ሊጠቀሙበት ይገባል።በአገልግሎት አሰጣጥ ላይ የሚታዩ በርካታ ችግሮች ስላሉ ሁሉም ተቋማት የአገልግሎት አሰጣጣቸውን ለማሻሻል ቴክኖሎጂውን ስራ ላይ ቢያውሉት ተጠቃሚ ይሆናሉ**

ቴክኖሎጂው ማሽኑ ከሚገኝበት ቦታ ውጭ (ከሌላ ቦታ) ሆኖ በማንኛውም ጊዜ አስተያየት ለመስጠት የሚያስችል ተጨማሪ እድልም ይሰጣል።ለተገልጋዮች እንዲታይ ተደርጎ በማሽኑ ላይ በተቀመጠው አድራሻ (ስልክ ቁጥሮች) አማካኝነት ተገልጋዮች ድምፃቸውን ቀርፀው በቴሌግራም፣ በሜሴንጀር፣ በኢሞና በሌሎች አማራጮች በኩል መላክ ይችላሉ።አስተያየቶቹ ወደ ኮምፒዩተር ስለሚተላለፉ የሚመለከተው አካል ለአስተያየቶቹ ምላሽ ይሰጣል።ከዚህ በተጨማሪም ይህ ቴክኖሎጂ ተገልጋዮች ስለተቋማት አገልግሎት ያላቸውን አስተያየት ብቻም ሳይሆን ጥያቄዎችን እንዲያቀርቡና የምክር አገልግሎቶችን እንዲያገኙም የሚያስችል ነው።ተገልጋዮች ራቅ ካለ ስፍራ ሆነው ጥያቄ አቅርበው ምላሽ ማግኘት ስለሚችሉ ፕሮግራማቸውን እንዲያስተካክሉ በማገዝ እንግልትን (አላስፈላጊ የጊዜና የገንዘብ ወጪን) ያስወግዳል።

ድምጽን መሰረት ያደረገ የሃሳብ መስጫ/መቀበያና የተገልጋዮች እርካታ መለኪያ በዓለም አቀፍ ደረጃም የተለመደ አይደለም።በአብዛኛው ተግባራዊ የሚደረገው አሰራር እጅግ በጣም ጥሩ (Excellent)፣ ጥሩ (Good) እና መጥፎ (Bad) በሚሉ መለኪያዎች ሃሳብ የመቀበል አሰራር ነው።በዚህም ምክንያት አሰራሩ ግልፅና ትክክለኛ የሆነ እንዲሁም የተብራራ መረጃ የመስጠት አቅም የለውም።ይህም የተቋማቱ የአገልግሎት አሰጣጥ ደረጃና የተገልጋዮች እርካታ በትክክል የት ላይ እንደሚገኝ አያመለክትም።

ድምጽን መሰረት ያደረገው የሃሳብ መስጫ/መቀበያ አሰራር ግን ሃሳብ/አስተያየት ሰጪው ሃሳቡን በሚሰማው የስሜት ደረጃ ልክ የመናገር እድል ይሰጠዋል።የደንበኞች/የተገልጋዮች የእርካታ ደረጃ በራሳቸው በተገልጋዮቹ አንደበት የሚገለፅ በመሆኑ ቴክኖሎጂው ግልፅና ትክክለኛ የሆነ እንዲሁም የተብራራ መረጃ የመስጠት አቅም እንዲኖረው ያደርገዋል።ይህም የተቋማቱ የአገልግሎት አሰጣጥ ደረጃና የተገልጋዮችና ደንበኞች እርካታ በትክክል የት ላይ እንደሚገኝና ምን ያህል እንደሆነ በግልፅ የማሳየት አቅም አለው።በዚህ ቴክኖሎጂ አስተያየቶቹን ማግኘት የሚችለው የተፈቀደለት አካል ብቻ ስለሆነ በቀላሉ የመጥፋት አደጋ አያጋጥማቸውም።ከዚህ በተጨማሪም ቴክኖሎጂው የተገልጋዮችን ነፃነትም ይጠብቃል።

ይህ ቴክኖሎጂ በበርካታ ተቋማት በአገልግሎት ላይ ያለውን የወረቀት አሰራር ወደ ዲጂታል የሚቀይር ሲሆን፤ ተቋማት የተገልጋዮቻቸውንና የደንበኞቻቸውን ሃሳብና አስተያየት መሰረት በማድረግ ክፍተቶች የሚታዩባቸውን አሰራሮቻቸውን በማስተካከልና ጠንካራ አፈፃፀሞቻቸውን በማጎልበት አገልግሎታቸውን እንዲያሻሽሉ ያግዛቸዋል።በሌላ በኩል ደግሞ ይህ አሰራር ተጠያቂነት እንዲሰፍንም እድል ይፈጥራል።ተገልጋዮች ላቀረቧቸው ሃሳቦች የሚያገኟቸው ግብረ መልሶች ‹‹እንዲህ ተብለን ነበር፤ ጉዳዩ ከምን ደረሰ?›› ብለው እንዲጠይቁ ያስችሏቸዋል።

እንደታምሩ ገለፃ፣ ወረቀትን መሰረት ያደረገው የሃሳብ መቀበያ ዘዴ ብዙ ጉድለቶች ያሉበት ሲሆን፣ የተገልጋዮችን የእጅ ጽሑፍ ለማንበብ አስቸጋሪ መሆኑ፣ አስተያየት ሰጪዎች ለአስተያየታቸው ምላሽ ማግኘታቸውን ማረጋገጥ አለመቻላቸው እንዲሁም አሰራሩ ሁሉንም ሰው አካታች አለመሆኑ ከጉድለቶቹ መካከል ጥቂቶቹ ናቸው።ወረቀት አልባው የተገልጋዮች የቅሬታ መቀበያና መልስ መላኪያ ቴክኖሎጂ ግን ሰዎች በድምፃቸው አስተያየታቸውን እንዲሰጡ የሚያደርግ በመሆኑ አስተያየቶችን በቀላሉ ለመቀበልና ለማዳመጥ ያስችላል።ቴክኖሎጂው በጊዜና በቦታ ያልተገደበ ስለሆነ ተገልጋዮች አስተያየታቸውን በጽሑፍ፣ በድምጽ፣ በምስልና በቪዲዮ ከየትኛውም ቦታ በየትኛውም ጊዜ ለሚፈልጉት ተቋም ለማድረስ ያስችላቸዋል።

ቴክኖሎጂው አነስተኛ ቦታ የሚፈልግና ከቦታ ቦታ መንቀሳቀስ የሚችል መሆኑም ሌላው የቴክኖሎጂውን ተመራጭነት የሚያጎላ ባህርይው ነው።ቴክኖሎጂው የቸኮሉ እንዲሁም ማየትና መፃፍ የተሳናቸው ተገልጋዮች አስተያየታቸውን እንዲሰጡ እድል የሚፈጥርም ነው።ታምሩ ይህን የፈጠራ ውጤት እንዲሰራ ምክንያት የሆነው ያ በአስተያየት መስጫው ላይ መፃፍ ባለመቻሉ ምክንያት በታምሩ እገዛ አስተያየቱ የተፃፈለት ግለሰብ፣ ዛሬ በዚህ ቴክኖሎጂ አማካኝነት ሃሳቡን መግለፅ እንደሚችል መገንዘብ አያዳግትም።

አንዱን ማሽን ለመግጠም 200ሺ ብር (ተጨማሪ እሴት ታክስ (ቫት)ን ጨምሮ) ወጪ የሚደረግበት ሲሆን፣ ቴክኖሎጂው በአሁኑ ወቅት በገቢዎች ሚኒስቴር የመካከለኛ ግብር ከፋዮች ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤት አገልግሎት እየሰጠ ይገኛል።

‹‹ሰዎች ቴክኖሎጂውን ተጠቅመው የሚሰጡት አስተያየት ያስደስተኛል›› የሚለው ታምሩ፣ የአስተያየት መስጫ ቴክኖሎጂው አሁን ያለበት ደረጃ ላይ እንዲደርስ ብዙ መሰናክሎችን እንዳለፈም ያስታውሳል።ተቋማትና ተገልጋዮች ስለቴክኖሎጂው ያላቸው ግንዛቤ ዝቅተኛ መሆኑ ቀደም ሲል ብቻም ሳይሆን፣ አሁንም ቴክኖሎጂውን ወደብዙ ተቋማት ለማስፋፋት እክል መፍጠሩን ይናገራል።

‹‹ወረቀትን መሰረት ባደረገ አሰራር ላይ ስለኖርን ወደ ዲጂታል ቴክኖሎጂ ለመግባትና ዘዴውን ለመልመድ የፍላጎት ማነስ ይስተዋላል።የተገልጋዮችን አስተያየት የማይቀበል ተቋም ውጤታማ ሊሆን አይችልም። ቴክኖሎጂው ቦታ የማይፈጅ፣ ብዙ መሰረተ ልማቶችን የማይጠይቅ፣ በቀላሉ መንቀሳቀስ የሚችልና ለአጠቃቀምም ቀላል በመሆኑ ተቋማት ሊጠቀሙበት ይገባል።በአገልግሎት አሰጣጥ ላይ የሚታዩ በርካታ ችግሮች ስላሉ ሁሉም ተቋማት የአገልግሎት አሰጣጣቸውን ለማሻሻል ቴክኖሎጂውን ስራ ላይ ቢያውሉት ተጠቃሚ ይሆናሉ።ተገልጋዮችም ሃሳባቸውን በነፃነት መስጠትን መልመድ አለባቸው።ተቋማቱ በእውነተኛ የተገልጋዮች ስሜት ላይ ተመስርተው አገልግሎት እንዲሰጡ ቴክኖሎጂውን እንዲጠቀሙበት ይመከራል›› ይላል።

በቀጣይም የምልክት ቋንቋንና ሌሎች ተጨማሪ አገልግሎቶችን በዚህ ቴክኖሎጂ ላይ በመጨመር አሁን ያለውን ቴክኖሎጂ ለማሻሻል እንደሚሰራ የሚናገረው ታምሩ፤ ቴክኖሎጂውን በሌሎች ተቋማትና በመላ ኢትዮጵያ ማስፋፋትና ለጎረቤት አገራት ጭምር እንዲዳረስ ማድረግ ቀጣይ እቅዱ እንደሆነም ይገልፃል።

# ወቅታዊ ትንታኔ

# ሰብዓዊ መብትን ለፖለቲካዊ አጀንዳ

አስቴር ኤልያስ

> **በኮሚሽኑ አማካይነት ይፋ የተደረገው የሰብአዊ መብት ‹‹ሪፖርት›› ለሰብአዊ መብት መከበር በመቆርቆር የተካሄደ ጥናት ሳይሆን በመንግስት ላይ ግልጽ የሆነ ፖለቲካዊ ጫና ለመፍጠር የታለመ መሆኑ እሙን ነው**

የተባበሩት መንግስታት የሰብአዊ መብት ባለሙያዎች ኮሚሽን ኢትዮጵያን አስመልክቶ ያወጣው ‹‹ሪፖርት›› ለሕወሓት የሽብር ቡድን በግልጽ ያደላ መሆኑን በመግለጽ የኢትዮጵያ መንግስት በ‹‹ሪፖርቱ›› ከማዘኑም በተጨማሪ ለሰብዓዊ መብት መከበር በመቆርቆር የወጣ ባለመሆኑ ውድቅ ማድረጉን አስታውቋል።

በወቅቱ ኮሚሽኑ ይፋ ያደረገው ‹‹ሪፖርት›› ግዴለሽነቱን የሚያሳይ መሆኑን ጠቅሶ ኢትዮጵያ ለሰላም ያላትን ቁርጠኝነት ከግምት ውስጥም ያላስገባ መሆኑን አመላክቷል። በተለይም ኮሚሽኑ በአሰራሩ በዋናነት ያነገበው የፖለቲካን ተልዕኮ ሲሆን፣ በኢትዮጵያ ላይ ፖለቲካዊ ጫና ለማሳደር ሲልም መንቀሳቀሱን በመግለጫው ጠቅሷል።

የመጀመሪያ ግኝት የሆነው የኮሚሽኑ ‹‹ሪፖርት ›› ይፋ የተደረገው በተባበሩት መንግሥታት ድርጅት የሰብዓዊ መብቶች ምክር ቤት፣ በኢትዮጵያ የእርስ በእርስ ጦርነት የተፈጸሙ ጥሰቶች አጣራለሁ በሚለው የሰብዓዊ መብቶች የባለሙያዎች ቡድን ነው።

የወጣው ‹‹ ሪፖርቱ›› በትክክል ለሰብዓዊ መብት በመቆርቆር የሰብዓዊ መብት ማስከበርን ያለመ ወይንስ መርዙን በማር ሸፍኖ የቀረበ ነው ሲል ያነጋገራቸው የኢፌዴሪ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አባል ዶክተር ፍቃዱ መንግስቱ፣ በመጀመሪያውኑ ኮሚሽኑ ያወጣው ሪፖርት በትክክል የተሟላ ባለመሆኑ ትክክለኛ ሪፖርት ነው ብሎ መወሰድ የሚቸግር መሆኑን ይናገራሉ። እንዲህም ሲባል አንደኛ የሪፖርቱ የአሰራር ዘዴ ትክክለኛ አካሄድን የተከተለ አይደለም።

ለዚህ ምክንያታቸው ደግሞ እርሳቸው ይፋ የተደረገውን ጥናት እንዳዩት ከሆነ በመጀመሪያ ሪፖርቱ ሲዘጋጅ ችግሩ የተከሰተባቸውን አካባቢዎች ሙሉ በሙሉ ወይም ደግሞ በተቻለው መጠን ሸፍኗል ወይ የሚል ጥያቄ እንዲያነሱ እንዳስገደዳቸው ያመለክታሉ። ከዚህ አንጻር ችግሩ የተከሰተባቸውን አካባቢዎች በተለይ አማራ እና አፋር ሆነው ሳለ በአግባቡ አለመዳሰሳቸውን ያስረዳሉ።

እርሳቸው እንደሚሉት፤ ለሰብዓዊ መብት በመቆርቆር የሚሰራው ስራ ለሁሉም እኩልነትን የሚያሳይ መሆን ይጠበቅበታል። ኮሚሽኑ ይፋ ባደረገው ሪፖርት ላይ ግን ከዚህ አኳያ በተለይ በትግራይ ክልል ዳር እስከዳር የዳሰሰ ሲሆን፣ ችግሩ ገዝፏል ሲልም ያነሳል። በሪፖርቱ ላይ የታዘቡት እውነታ ግን ኮሚሽኑ የትግራይ ክልልን ያህል የሌሎቹንም አካባቢዎች ያልሸፈነ መሆኑን ነው።

ዶክተር ፍቃዱ፣ ኮሚሽኑ ያወጣውን ሪፖርቱ ካስተዋሉ በኋላ በሁለተኛ ደረጃ ጥያቄ የፈጠረባቸው ነገር ችግሩ የደረሰባቸውን ሰዎች አጥኚዎቹ ቡድኖች ያገኙት እንዴት ነው የሚለው ነው። ተጎጂዎቹን ያናገሯቸውስ በምን አይነት ሁኔታ ነው ሲሉም ያክላሉ። መረጃው የተገኘው በስልክ ብቻ ነው ወይ የሚለው ግልጽ መሆን እንዳለበትም ነው የሚናገሩት። እርሳቸው፣ ችግር የደረሰባቸውን ሰዎች በተቻለ መጠን በአካል ሊያገኟቸው ይገባል የሚል አስተያየት አላቸው። ከዚህ የተነሳ ሪፖርቱ ትክክለኛውን መረጃ ይዞ ተጠናቅሮ የቀረበ ነው ለማለት እንደሚቸገሩ ያስረዳሉ።

ሌላው ሪፖርቱ ለሰብዓዊ መብት በመቆርቆር የተሰራ አይደለም ሲሉ የጠቀሱት ደግሞ፤ ራሳቸው አጥኚዎቹ የችግሩ ተጋላጭ ናቸው ብለው የወሰዷቸውን ሰዎች 185 አካባቢ ነው ብለዋል። ነገር ግን አሁን ካለው የመሬት አቀማመጥ ከችግሩ ግዝፈት እና ስፋት አንጻር ወስደናል ባሉት ናሙና ብቻ ድምዳሜ ላይ መደረሱ ትክክል መስሎ አልታየኝም ብለዋል። ከዚህ አንጻር ሪፖርቱ በትክክል የተሰራ ነው አሊያም የችግሩን ሙሉ ስዕል የሚያሳይ ሪፖርት ነው ብሎ ለመቀበል አልደፈሩም።

የኦሮሞ ነጻነት ግንባር (ኦነግ) አማካሪ አቶ ኢብሳ ነጋዎ በበኩላቸው፤ የዓለም አቀፉ የሰብአዊ መብት ኮሚሽን የባለሙያዎች ቡድን በኢትዮጵያ ላይ አካሂጄዋለሁ ያለው ‹‹ሪፖርት›› አግባብነት የሌለው መሆኑን ይናገራሉ። በዚህ አካል ተጠንቶ የቀረበው ሪፖርት አነሳሱ ራሱ የፖለቲካ ቅኝት ያለው ነው። በመጀመሪያ የሰብዓዊ መብት ጥሰትን የሚያሳይ ጥናት ለመሆኑ ሕጋዊና ሙያዊ ሊሆን ይገባው ነበር፤ ነገር ግን ይህን ሳይንሳዊ አካሄድ የተከተለ አይደለም ይሞግታሉ።

በተለይ የሪፖርቱ ዓላማ በእርዳታ ብሎም በሰብአዊ መብት ስም የሚደረግ አካሄድና በመንግስት ላይ ጫና ለማሳደር የታሰበ ሴራ ነው። በቁጥር አነስተኛ የሆኑ አካላት በስልክ አነጋግሮ ብቻ ሪፖርት ይፋ ማድረግ በእርግጥም የሚያስገርም ነው ብለዋል። ሌላው በአፋር እና በአማራ ክልል የተገደሉ ንጹኃን ዜጎች፣ የተደፈሩ ሴቶች፣ የተቃጠሉ መሰረተ ልማቶች ከግምት ውስጥ አልገቡም፤ ሌላው ቀርቶ በጋሊኮማ ብቻ የደረሰው አሰቃቂ የዘር ማጥፋት ግፍ በቂ ነበር። ሆኖም ግን በዚህ በኩል ያለውን የሰብአዊ መብት ጥሰት ማንሳት አልተፈለገም። ይህም ሆን ተብሎ በኢትዮጵያ መንግስት ላይ ጫና ለማሳደር ሲባል የተደረገ እንጂ በእርግጥ ኮሚሽኑ ለሰብዓዊ መብት ተቆርቁሮ ያጠናው እንዳልሆነ ነው የሚገባኝ። በመሆኑም ኮሚሽኑ አካሄድኩት ያለው ምርመራ ትክክለኛውን መንገድ የተከተለ ሳይሆን አድሏዊ ነው ለማለት ያስገድዳል።

በመላው ዓለም የሚገኙ የኢትዮጵያ ዳያስፖራ አደረጃጀት አባላት ጥምረት፣ ለተባበሩት መንግስታት ከፍተኛ የሰብአዊ መብቶች ኮሚሽነርና ለተባበሩት መንግስታት የሰብአዊ መብቶች ኮሚሽን ምክር ቤት አባል አገራት በጻፈው ደብዳቤ፤ በኢትዮጵያ የሰብአዊ መብቶች ጉዳይን እንዲመረምር የተሰየመው ዓለም አቀፉ የሰብዓዊ መብቶች ባለሙያዎች ቡድን የተቋቋመበት እሳቤ በተሳሳቱ መነሻዎች ላይ የተመሰረተ ነው ማለቱን ከጥምረቱ ድረገጽ የተገኘው መረጃ ያመለክታል። የተቋቋመውም ቡድን ሊፈርስ እንደሚገባም ነው ጥምረቱ በጻፈው ደብዳቤ የጠየቀው። ለዚህም በምክንያትነት ያስቀመጠው በኢትዮጵያ የሰብአዊ መብቶችን ጉዳይ እንዲመረምር የተሰየመው ዓለም አቀፉ የሰብዓዊ መብቶች ባለሙያዎች ቡድን የፖለቲካ ዓላማ ያለውና ከደረጃ በታች የሆነ፣ የጉዳዩን አሳሳቢነት የማይመጥንና አንድን ወገን ብቻ ለይቶ ማጥቃትን ዓላማ ያደረገ አደገኛ ሪፖርት ይዞ መውጣቱ ነው። አባል አገራት ይህን የተሳሳተ ሰነድ በፊርማቸው ከማጽደቅ እንዲቆጠቡም ጥምረቱ ጠይቋል። ይልቁኑ አባል አገራቱ በኢትዮጵያ ለተጎጂዎች ዘላቂ ፍትሕ ለማስገኘትና ጥበቃ ለማድረግ የተጀመረውን ሂደት ሊደግፉ ይገባል ብሏል።

እንዲያውም አባል አገራቱ፣ በኢትዮጵያ የሰብአዊ መብቶችን ጉዳይ እንዲመረምር የተሰየመው የባለሙያዎች ቡድን ያቀረበው ሪፖርት ለአንድ ወገን ያደላና ፖለቲካዊ ዓላማን ያነገበ በመሆኑ ያቀረበውን ሪፖርት ውድቅ እንዲያደርጉና ኮሚሽኑንም እንዲያፈርሱ ጥምረቱ በጻፈው ደብዳቤ ጠይቋል። በተጨማሪም አባል አገራቱ ከኢትዮጵያ መንግስት ጋር በቅርበት በመስራትና የኢትዮጵያን ሉዓላዊነትን በማክበር የፍትሕ ስርዓቱ አቅም እንዲገነባ እንዲሁም በአማራ፣ አፋርና በትግራይ ክልሎች ተፈጽመዋል የተባሉ የሰብአዊ መብት ጥሰቶች በገለልተኝነት እንዲመረምሩ የኢትዮጵያን ፍትሕ አካላት እንዲያግዙ ጥያቄውን አቅርቧል።

የዲፕሎማሲና ዓለም አቀፍ ግንኙነት መምህር አቶ እንዳለ ንጉሴ በበኩላቸው፤ ሪፖርቱን ያዘጋጀው ኮሚቴው ከመጀመሪያው ጀምሮ በራሱ ሕገ ወጥ ነው ይላሉ። አካሄዳቸው በኢትዮጵያ ላይ ግልጽ የሆነ ጫና ለመፍጠር የተደረገ መሆኑን የሚያሳይ እንጂ ለሰብዓዊ መብት በመቆርቆር የተጠና አለመሆኑን ይናገራሉ። ሪፖርቱ በዚህ ልክ በሐሰት ድርሰት የተደራጀ ከመሆኑም በተጨማሪ እየተሰራ ያለውም በባለሙያዎች ሆን ተብሎ እንደሆነ ያመላክታሉ። ነገር ግን አሳዛኙ ነገር ሙያዊ አካሄድን የተከተለ አለመሆኑ ብሎም ግዴታውንም ያልተወጣ ጥናት መሆኑ ነው ሲሉ ያስረዳሉ።

ስለዚህ ይላሉ አቶ እንዳለ፣ ሪፖርቱ እንደሪፖርት ሊቆጠር አይችልም። ምክንያቱም አንደኛ ሳይንሳዊ ዘዴን አልተከተለም፤ ሁለተኛ ደግሞ መሳተፍ የሚገባቸውን ባለድርሻ አካላት አልተሳተፉበትም። ስለሆነም በሶስት ሰው የተሰራ ሪፖርት የ120 ሚሊዮን ሕዝብ አገር የሆነችውን ኢትዮጵያ አይመጥንም፤ በአፍሪካ ትልቋን ኢትዮጵያ፣ በጥቅል ነገሯ ስትወሰድ ደግሞ በአፍሪካ ቀዳሚ የሆነችውን አገር እንዲሁም ጂኦፖለቲካዊው ድርሻዋ ከፍ ያለችውን አገር በእነዚህ ሶስት ሰዎች መወከል አይገባትም።

እርሳቸው እንዳሉት፤ የአሜሪካ የልማት ተራድኦ ድርጅት (ዩ.ኤስ.ኤ.አይ.ዲ) እርዳታን ለመላ ኢትዮጵያ ከመስጠት ይልቅ እየመረጠ የሚሰጠው ለአሸባሪው ቡድን ነው። ይህ ማለት ጥፋት ለሚፈጽም ቡድን መስጠት ማለት ነው። ለስንት ዓመታት የሚመጣለት እርዳታ እየሸጠ መሳሪያ ሲገዛበት የነበረው በተመቻቸለት መንገድ ነው። ይህ አሸባሪው ቡድን ሲዘርፍ አይናቸው ያያል። ነዳጁን፣ ዘይቱን፣ ስንዴውን ከነመኪናው ጭምር ሲዘርፍ አንዱ ላይ እንኳን ስለዘራፊነቱ አላነሱም። እንዲያውም ከምስረታው ጀምሮ እርዳታን፣ ረሃብን እንደጦርነት የተጠቀመው ቡድን ቢኖር ሕወሓት ነው ሲሉ ይናገራሉ።

ዶክተር ፍቃዱ በበኩላቸው፤ ሪፖርቱ ማካተት የተገባውን ሁሉ አካትቶ ካለመሰራቱ በተጨማሪ ዋና ዓላማው ችግርን ወደ አንድ ወገን እንዲያመዝን አድርጎ ለማሳየት መጣሩ ነው፤ ይህ ደግሞ ትክክል አይደለም። ምክያቱም የሪፖርቱ ዋና ዓላማ ለሰብዓዊ መብት መቆርቆርን የሚያሳይ ሳይሆን በኢትዮጵያ መንግስት ላይ ፖለቲካዊ ተጽዕኖ ለማሳደር ነው ብለዋል።

የኮሚሽኑ ሪፖርት በአንድ ወገን ላይ ተጽዕኖ ከማሳደር ውጪ የችግሩን መሰረት በመዳሰስ እና መካተት የተገባቸው ተካትተው ባለመገኘታቸው የጥናቱን አካሄድ ሙሉ የሚያደርገው ሆኖ አላገኙትም። ጥናቱ የተሟላ ካለመሆኑም በተጨማሪ አንዱን የመደገፍ ሌላውን የማንኳሰስ አካሄድን የተከተለ ነው። ስለዚህም የሪፖርቱ አካሄድ በእርግጥም ለሰብዓዊ መብት በመቆርቆር የታሰበ አይደለም፤ እንደዛ ቢሆን ኖሮ ትክክለኛ የሰብዓዊ መብት ጥሰት ሳይንሳዊ አጠናን የተከተለ አካሄድ ይዞ ይነሳ ነበር። ነገር ግን ወደ ችግሩ ተጠግተው ግራና ቀኙን በእኩል ማየት እየተጠበቀባቸው ያንን ግን አላደረጉም። መልካም ይሆን የነበረው ችግሩ በተከሰተባቸው አካባቢዎች በመገኘት በአግባቡ መረዳት ቢችሉ ነበር። ዝም ብሎ ሪፖርት ነው በሚል ብቻ አንዱን አንስቶ ሌላውን ለመጣል የታለመ ከሆነ ግን አግባብ አይደለም። በመሆኑም ይህን ሪፖርት በንጽጽር የተሰራ ሪፖርት ነው ብለው አይወስዱም።

መረጃዎች እንደሚያመለክቱት፤ አሸባሪው ሕወሓት ገና አንድ ብሎ ሲጀምር የሰሜን እዝን ከጀርባው በመውጋት እንደሆነ ይታወሳል። የመከላከያ ሰራዊትን በማጥቃት የጀመረው ጥቃት አንድ ሁለት እያለ መንግስት የዘረጋለትን የሰላም እጅ አልቀበልም በማለት ወደሶስተኛው ጦርነት አሻፈረኝ ብሎ መግባቱም ይታወቃል።በዚህም በአማራና በአፋር ክልል የፈጸማቸው ግፎች በርካታ ሲሆን፣ በተለይ ህጻናትንና በእድሜ የገፉትን እናቶችን ከመድፈር እስከማዋረድና መሽማቀቅ መድረሱ ይታወሳል። የመሰረተ ልማቶችን በተለይም የትምህርት እና የጤና ተቋማትን ከማፍረስ እስከማቃጠል የተሳተፈበት ተግባሩ እንደሆነም እሙን ነው። ይህ ሁሉ በአሸባሪው ሕወሓት አማካይነት በሰብዓዊነት ላይ የተፈጸመ ወንጀል ነው።


የሽብር ቡድኑ የኢትዮጵያ የግዛት አንድነትና ሉዓላዊነት አደጋ ላይ ለመጣል ዳግም ጦርነት መክፈቱ፣ የሰብአዊ እርዳታ ተሽከርካሪዎችን ለጦርነት መጠቀሙ እና ለሰብአዊ እርዳታ የተዘጋጀ ነዳጅ ላይ ዝርፊያ መፈጸሙ በተደጋጋሚ መነገሩ ይታወሳል። ይሁንና ዓለም አቀፍ ተቋማት በሽብር ቡድኑ የተፈጸሙና ዓለም አቀፍ ህጎችን የጣሱ ወንጀሎችን ማጣራት ሲገባቸው ቸል መባሉ ሳያንስ ይባስ ብሎ የተባበሩት መንግስታት የሰብአዊ መብት ባለሙያዎች ኮሚሽን ለሕወሓት የሽብር ቡድን በግልጽ ያደላ ሪፖርት ይፋ ማድረጉ የኢትዮጵያን መንግስት ማሳዘኑ ይታወቃል።

እንደ አቶ እንዳለ አባባል፤ ኢትዮጵያውያን ለተሳሳተ ፕሮፓጋንዳ እጅ መስጠት የለባቸውም። ለእንዲህ አይነቱም ውዥንብር ቦታ መስጠት አያስፈልግም። ነገር ግን ሁሉም ዜጎች ባገኙት አጋጣሚ ሁሉ የረከሰ ሪፖርት ስለመሆኑ መግለጽ ይጠበቅባቸዋል። ከወትሮ በተሻለ የበለጠ አንድነትን በማጠናከር እንዲህ አይነቱን ተራ ትርክትን መከላከል መቻል አስፈላጊ ነው። በውጭ አገር ያሉ ኢትዮጵያውያንና ትውልደ ኢትዮጵያውያንም ባገኙት አጋጣሚ ሁሉ ተገቢነት የሌለው ሪፖርት ከመሆኑም በላይ የረከሰ ሪፖርት መሆኑን ሊያስገነዝቡ፤ ተገቢም አለመሆኑን ሊያሳውቁ ይገባቸዋል። በአሁኑ ወቅት በአማራው፣ በአፋሩ የደረሰውንና እየደረሰ ያለውን ጉዳት ማስረዳትም ይጠበቃል።

በኮሚሽኑ አማካይነት ይፋ የተደረገው የሰብአዊ መብት ‹‹ሪፖርት›› ለሰብአዊ መብት መከበር በመቆርቆር የተካሄደ ጥናት ሳይሆን በመንግስት ላይ ግልጽ የሆነ ፖለቲካዊ ጫና ለመፍጠር የታለመ መሆኑ እሙን ነው። በዚህም አካሄዱ በኢትዮጵያ ደካማ መንግስት በማስቀመጥ አገሪቱን ባሻቸው ልክ ለማሽከርከርም የታቀደ በመሆኑ ሕልማቸው እውን እንዳይሆን ከወዲሁ አንድነትንና መግባባትን ማጠናከሩ የግድ ይሆናል። የእርስ በእርስ አለመግባባት የሚኖር ከሆነ ግን በበሬ ወለደ ሪፖርታቸው አንዱን ብሔር ወይም ኃይማኖት በአንደኛው ላይ በማነሳሳት ምኞታቸውን እውን ሊያደርጉ ይችላሉና ሁሉም ዜጋ ንቁ ሊሆን ይገባል።

ማህበራዊ

# ሴቶች


ወጣት ፌቨን የኋላሸት


ወይዘሮ ሀናን ታዬ


ወይዘሮ ኩሪ ኃይሉ

# ሴቶችና የኢሬቻ በዓል

**ሰላማዊት ውቤ**

ኢሬቻ አንድ ሰው በመጀመሪያ ከራሱ ጋር ከዚያ በቅርቡ ካለው ከጎረቤቱ ጋር ከዚያም ከማኅበረሰቡ ጋር በመጨረሻም ከተፈጥሮ ጋር እርቅ የሚያወርድበት በዓል መሆኑ ይነገራል። ሰዎችን በማሰባሰብ አንድነትን የሚሰብክ የሰላም ተምሳሌት መሆኑም ይጠቀሳል ። የሰላም ተምሳሌት የሆኑት ሴቶች “መሬሆ”“ መሬሆ ” በማለት ትከሻ ለትከሻ ተቃቅፈው ለፈጣሪያቸው ውዳሴ ያቀርቡበታል።

ውዳሴውን የሚያቀርቡት በተለያዩ አካባቢ ባሉ የኦሮሞ ባህላዊ አልባሳት ተውበውና አሸብርቀው ነው ። ከቱባው ባህል መገኛ አንዱ በሆነው አርሲ የመጣችውና ኢሬቻን በአዲስ አበባ ስታከብር ያገኘናት ወጣት ፌቨን የኋላሸት ኢሬቻ የሰላም፣ የፍቅርና አብሮነት በዓል መሆኑን ትናገራለች።

ወጣት ፌቨን ኢሬቻን ሴቶች እርስ በእርሳቸው ትከሻ ለትከሻ ተቃቅፈው ለምለም ሳርና አደይ አበባ በመያዝ “መሬሆ” “መሬሆ” እያሉ በሐይቅ፣ በወንዝ፣ በምንጭና በውሃ ዳርቻ እንዲሁ እንደ አዲስ አበባው በደመቀ የሚያከብሩበት ስርዓት ላይ የመሳተፍ ዕድል ማግኘቷንም ታወሳለች።

‹ኢሬቻ የኦሮሞ ሕዝብ ከገዳ ሥርዓት ከወረሳቸው ትሩፋቶች አንዱ ነው። የክረምቱን ድቅድቅ ጨለማ አልፎ የፀደይ ብርሃን ወቅት ሲገባ ክረምቱን ያሳለፈ፣ ሰብልን ያበቀለ፣ ማሳውን ያለመለመ ፈጣሪውን ማመስገኛ ስነስርዓት ይካሄድበታል። እርቅ፣ አንድነት፣ ሰላምና መተሳሰብ በስፋት ይሰበክበታል ። መጀመሪያውኑ ሰው ከራሱ ጀምሮ በየደረጃው እርቅ ሳያወርድ ኢሬቻ አይከበርም›› የምትለው ወጣቷ በኦሮሞ ባህል ዘንድ ከፍተኛ ሚና ያለውና ሴቶች መሪ ተዋናይ የሆኑበት ስንቄ ወይም ሲቆ የተሰኘው ባህላዊ የግጭት አፈታት ስርዓት የሚተገበርበትም እንደሆነ ታነሳለች።

ሲንቄ ሆሮሬሳ ከሚባልና ከሌሎች ከማይነቅዙ ከተመረጡ የዛፍ ዓይነቶች ተቆርጣ የምትዘጋጅ ቀጥ ያለችና ያልተጣመመች ዘንግ በትር ስትሆን የጋብቻ ዕለተ እናት ለምትድራት ልጇ የምትሰጣትና ልጅቱም እስከ ዕለተ ሞቷ የማትለያት የክብር መገለጫ ስጦታዋ ናት ትላለችም።

በመሆኑም ኢሬቻ ሴቶች ከዚሁ ጋር በተያያዘ በልዩ ሁኔታ ክብራቸውን የሚያስጠብቁበት፣ ሰላምን የሚያወሩድበት፣ የሚሰብኩበት፣ ፈጣሪን የሚለምኑበት በርካታ ተግባራትን የሚከውኑበት ባህላዊ ስርአት ነው ማለት ይቻላል። በተለይ ከዚሁ ሴቶች መሪ ተዋናይ በሆኑበትና ሚናቸውን በሚያጎላው ሲንቄ የተሰኘ ስያሜ በኦሮሞ ሕዝብ ሃደ ሲንቄ ተብለው ልዩ ክብርና ቦታ የሚሰጣቸው እናቶች በኢሬቻ በዓል ፈጣሪን ከማመስገን አልፈው ሕዝቡንና አገርን ይመርቁበታል። በበዓሉ ላይም ሕዝቡ ጥላቻን እንዲያርቅ እርስ በእርስ መተሳሰብን፣ አንድነትን፣ ሕብረትን እንዲያጠናክርና በጋራ በመቆም አገሩንና ወገኑን እንዲጠብቅ የየራሳቸውን መልዕክት ያስተላልፋሉ። ምስጋናንና ሰላምን የሚሰብኩና የሚያመለክቱ ሲንቄን ጨምሮ ትኩስ ወተት፣ ጭኮ፣ ለምለም ቄጤማና አበባ ይዘው ይመጣሉ። በዓሉ ለበርካታ ሺህ ዘመናት በዚህ መልኩ ሲከበር እንደቆየ ለቀጣዩ ትውልድም በዚህ መልኩ ማስተላለፍ እንደሚገባ በማሳሰብ ያከብሩታል።

ወጣቷ እንደምትለው ከዚህ አንፃር እሷና ሌሎች ወጣት ሴቶች በዓሉን ለማስቀጠልና ባህሉን ሳይለቅ እንዲከበር ለማድረግ በርካታ ሥራዎችን ሲሰሩ ቆይተዋል ።

ስለ ኢሬቻ በዓል ብዙ ነገሮች ሲወሩ መኖራቸውን ያስታወሰችው ወጣቷ አንዱ በዓሉን ከባእድ እምልኮና ከተለያዩ ነገሮች ጋር ተያይዞ ሲነዛ የነበረው ወሬ መሆኑን እንደማሳያ ታነሳለች። አንዳንድ ሴቶች በተለይም በዕድሜ ትልልቅ የሆኑ እንዲሁም የቀለም ትምህርት ያልቀሰሙና ስለ በዓሉ ብዙም ግንዛቤ የሌላቸው እናቶች ዛፍ ቅቤ ሊቀቡ፣ በሥሩም ቡና ሊያፈሉ፣ በስለታቸው መሰረትም ሐይቅ ውስጥ ሽቶ ወይም አረቂ ይረጫሉ ሲባል መስማቷንም ታወሳለች። ይሄ እየተጋነነ ወሬ ነው ባይ ነች ።

በተለይ በቢሾፍቱ አርሰዲ ሐይቅ የሚከበርበት ሁኔታ ቆሪጥ ከሚባል ያልተጨበጠ መንፈስን እንደማምለክ ተደርጎ በመውሰድ በዓሉ በሀሜት የሚብጠለጠልበት ሁኔታም አለም ትላለች ። እንደ ፌቨን እንዲህ ዓይነቱ አስተሳሰብ ከሌሎች ሰዎች ብቻ ሳይሆን የሚንፀባረቀው ከራሱ ከአንዳንድ የኦሮሞ ተወላጅ ጭምር ነው። እሷም ይሄንን እየሰማች እንደ ማደጓ እስከ ቅርብ ዓመታት ድረስ እንዲህ ዓይነት አስተሳሰብ ነበራት። ይሄ ኢሬቻ በስፋት እንዳይከበር፣ እንዳይተዋወቅ፣ የራሱ ጫና ሲፈጥር ቆይቷል ብላ ታስባለች። በቱሪስት መስህብነቱ ለኦሮሚያ ክልልም ሆነ ለአገር ሊያስገኝ የሚችለውንም ከፍተኛ ገቢ ሳያስገኝ ቀርቷልም ስትል ተፅዕኖውን ትገልፀዋለች ።

እንዲህ ዓይነቱ ከበዓድ አስተሳሰብ ጋር የተያያዘ ሀሜት በዓሉ ምንነቱ ጎልቶ እንዳይንፀባረቅም ተፅዕኖ አድርጓል። ‹ይቅርታ አድርጉልኝና የበዓሉ ባለቤት በነፃነት እንዳያከብረው ወይም እንዲሸማቀቅ ሳያደርገውም የቀረ አይመስለኝም › ትላለች ወጣቷ ። አሁን ላይ በተለይም በአዲስ አበባ መከበር ከጀመረ ወዲህ እንዲህ ዓይነቱ አስተሳሰብ እየተቀየረ መጥቷል። እሷን ጨምሮ ብዙዎች በተለይም ወጣቶችና ሴቶች ጥሩ ግንዛቤ እያገኙ ነው። ዘንድሮ ደግሞ ለአራተኛ ጊዜ ሲከበር ኢሬቻ ከእንዲህ ዓይነቱ ባአድ አምልኮ ጋር በፍፁም የማይገናኝ ባህል መሆኑ ታውቆና ተረጋግጧል ማለት ይቻላል ስትል ትናገራለች።

ባህል የሆነው ኢሬቻ እሷንና ሌሎች ወጣቶችን ጨምሮ በበርካታ ማህበረሰብ ዘንድ ተገቢ ግንዛቤ ተይዞበታል ። እነሱም በበዓሉ ዙርያ አንዱ ተልኳቸው በሕዝቡ ውስጥ እንዲህ ዓይነቱን ትክክለኛ አስተሳሰብና አመለካከት እንዲፈጠር ማስቻል ነው። በዘንድሮ በዓልም በተለይ በአዲስ አበባ ለአራተኛ ጊዜ በተከበረው ወጣቶች ይሄን ግንዛቤ ፈጥረናል ብላ ታስባለች። በመሆኑም እንደማንኛውም በዓላት የተለያዩ የሕብረተሰብ ክፍሎች በነቂስ ወጥተው ሊያከብሩት መቻላቸውን ለመመልከት በቅተናልም ብላለች።

ሥራውን ሲያከናውኑ የቆዩት በዋነኝነት በሴቶች አማካኝነት ለበዓሉ ከሚደረግ የባህላዊ ምግብና መጠጥ ዝግጅት ጎን ለጎን መሆኑንም ገልፀልናለች። ለበዓሉ በሴቶች በርካታ ባህላዊ መጠጦችና ምግቦች እንደሚዘጋጁና ሴቶች በዚህ ወቅት ከወትሮው ለየት ባለ ሁኔታ በሥራ እንደሚጠመዱም አውግታናለች። በወቅቱ ከሚዘጋጀው ምግብ በማር ብቻ የሚጣል ጠጅ ዋናው እንደሆነም አውግታናለች። ጠጁን የሚጥሉት በአካባቢው በጠጅ ሙያ አንቱ የተባሉ እናቶች እንደሆኑና ጠጅ የመጣል ዝግጅቱም በዓሉ ከመድረሱ ቀደም ብሎ እንደሚጀመርም አጫውታናለች።

በአብዛኛው ይሄ ደረቅ ጠጅ እንደ አባ ገዳ ላሉ ለተከበሩና በማህበረሰቡ ዘንድ ትልቅ ቦታ ለሚሰጣቸውና አንቱ ለተሰኙ ሰዎች እንዲሁ በአዋቂ ዕድሜ ደረጃ ላሉ የሚዘጋጅ መሆኑንም ነግራናለች። በበዓሉ በተለይ ለወጣትና ታዳጊ ልጆች እንዲሁም የማር ብርዝ እንደሚዘጋጅ ታነሳለች። ለኢሬቻ በዓል ከሚዘጋጁ ባህላዊ ምግቦች መካከል ቡነቀላ፣ የአንጮቴ ገንፎ ፣ ቂንጬ እንደሚያዘጋጁና ሁሉም የሚዘጋጁት በቅቤ እንደሆነም አጫውተናለች። ቡነቀላ ምግብ ከጠጅ ጋር አብሮ እንደሚቀርብም ታስረዳለች። የከብት እርድ ስርዓት እንደሚከናወንም ነግራናለች።

ኢሬቻ ከኢትዮጵያውያን ውጪ ሌሎች የዓለም አገራት የሌላቸው ባህል እንደመሆኑ በአንድነት ማክበርና ለሌሎች ዓለማት ማስተዋወቅ ይገባል። ባህላዊ ቅርፁን ሳይለቅ በቱሪስት መስብዕነቱ እንዲቀጥልና የኢኮኖሚ ምንጭ በመሆንም በአገሪቱ ዕድገት የበኩሉን ድርሻ ኢንዲወጣ ኢትዮጵያውያን በሙሉ በጋራ መሥራት እንዳለባቸውም መልዕክት ታስተላልፋለች።‹‹ አያቶቻችን በዓሉን በዚህ በባህላዊ መልኩ ነበር የሚያከብሩት እኛም ዘንድሮ በዚሁ መልክ ነው ያከበርነው ። ይሄ በጎ የምስጋና ስርዓትም ከትውልድ ትውልድ እየተሸጋገረ ይቀጥላል›› ስትልም አስተያየቷን ትቋጫለች ወጣቷ የአርሲ ተወላጅ ፌቨን ።

‹‹ተተኪ ወጣት ሴቶች የባህላዊ ምግብ ዝግጅቶቹን ከእኛ ከእናቶችና ከአያቶቻችን መማር አለባቸው። ምክንያቱም አሁን በዓሉ ከኦሮሞ ሕዝብ አልፎ እንደ አገር ብሎም የዓለም ኃብት ሆኗል ››ያሉን ደግሞ ሌላዋ አስተያየት ሰጪ ወይዘሮ ሀናን ታዬ ናቸው ።

እንደ ወይዘሮዋ ሴቶች ከእናቶቻቸውና አያቶቻቸው የወረሱትን የኢሬቻን በዓል ባህላዊ ምግብ ዝግጅት ለተተኪ ወጣት ሴቶች ያሳዩበት ሁኔታ አለ። ይሄ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በሚገኙ በ10ሩም ክፍለ ከተሞች በ121 ወረዳዎች ወርዶ በመተግበሩ ኢሬቻ በዓል ባህሉን ጠብቆ ለዓለም ቅርስነት በሚመጥን መልኩ መከበር አስችሏል። በዚህ መልኩ ለበዓሉ የተዘጋጀውን ባህላዊ ምግብና መጠጥ በውጪ ቱሪስቶች መስህብ ሆኖ መደነቅም ችሏል። በተለያየ የኦሮሚያ ክልል የሚገኙ ባህላዊ አለባበሶችም የበዓሉ አንዱ አካል ነበሩ። ወንዶችና ሴቶች፣ ወጣቶችና ህፃናት በተለይም አረጋውያን በዚህ ዓይነቱ በዓመት አንዴ አንዳንዴም ሁለቴ በሚለበስ የባህል ልብስ እንዲያሸበርቁና አደባባይ ወጥተው በዓሉን እንዲያከብሩት ተሰርቷል። ምክንያቱም አሁን በዓሉ የኦሮሞ ብቻ ሳይሆን የመላው ኢትዮጵያና የዓለም ሆኗልና ነው። ዘንድሮ አዲስ አበባ ላይ የተለያየ ብሄር ቅልቅል ባለው ሕዝብ በዓሉ የሁላችንም ነው በሚል ስሜት መከበሩንም አስተውለዋል።

ክትፎ፣ ጭኮ ፣ አነባበሮ፣ በቅቤና በርበሬ የተለወሰ ቆሎና በሌሎች የኦሮሞ ባህላዊ ምግቦች ዝግጅት በዓሉ መከበሩን ያወሱት ሌላኛዋ እንግዳ ወይዘሮ ኩሪ ኃይሉ እንደተናገሩት በዕለቱ እያከበሩት ያለው የኢሬቻ በዓል የመጀመሪያቸው አይደለም። ኢሬቻን ለረጅም ጊዜ ሲያከብሩ ቆይተዋል። በዓሉ በአዲስ አበባ በደማቅ ሁኔታ መከበር ከጀመረ አራተኛ ዓመቱን የያዘ ሲሆን እሳቸው አራቱንም ዓመት ተገኝተው አክብረውታል። በዓሉ የሚከበረው የኦሮሞ ቤሄረሰብ ባህል ብቻ በመሆኑ ሳይሆን የኢትዮጵያውያኖች ባህል ጭምር ሆኗል ብለዋል።

ወይዘሮ ኩሪ ኃይሉ እንደ ብሄረሰቡ አባልነታቸው ይሄ ግንዛቤ በሁሉም ኢትዮጵያዊያን ዘንድ እንዲሰርጽና በዓሉን በነቂስ ወጥቶ እንዲያከብር መሰራት አለበት ይላሉ። ኢሬቻ ማለት ሰላም፣ ፍቅር፣ አንድነትና ወንድማማችነት እህትማማችነት ማለት ነው። የኦሮሞ ቤሄረሰብም ከጨለማው ዘመን ወደ ብርሃናማው ዘመን በሰላም ስላሸጋገረው አምላኩን የሚያመሰግንበት፣ እርጥብ ቄጤማ ይዞና ሐይቅ ዳርቻ ሆኖ ለአምላኩም ምስጋናውን የሚያቀርብበት ነው። መጪውና ቀሪው ዘመኑ የተባረከና የተቀደሰ እንዲሆን ፈጣሪውን የሚለምንበትም በዓል ነው ብለዋል።

ወይዘሮ ኩሪ እንደነገሩን ለዚህ በዓል ሴቶች በልዩ ሁኔታ ዝግጅት አድርገናል። በአዲስ አበባ ዙሪያ በአራቱም በሮች በመግባት ወደ መስቀል አደባባይ የሚጓዙትን እንግዶችን ለማስተናገድ በቂ ዝግጅቶች በመደረጋቸው የመጡት እግዶች ተደስተው ተመልሰዋል። እኛም እንዳስተዋልነው በዓሉን ለማክበር ወደ መስቀል አደባባይ የሚጎርፈውም ሆነ ከመስቀል አደባባይ በዓሉን እያከበረ የሚመለሰው የተዘጋጀውን ማዕድ በጋራ እንዲመገብ ተደርጓል። በአንዳንድ የሰው ንክኪ በሚበዛባቸውና ለኮረና መተላለፍ መነሻ ይሆናሉ በተባሉ ቦታዎች ደግሞ ዳቦ፣ ዳቦ ቆሎ፣ ቆሎ፣ ውሃና ሌሎች ደረቅ ምግቦችን የሚመገቡበት ሁኔታ እንዳለ መታዘብ ችለናል።

# ማረፊያ

## አዲስ ዘመን ድሮ

ኃይለማርያም ወንድሙ

**በዛሬው የአዲስ ዘመን ድሮ ዓምዳችን በ1944 በአዲስ ዓመት ማግስት የታተሙ ጋዜጦችን ቃኝተናል። ከተመለከትናቸውና ቀልባችንን ከሳቡ የጋዜጣው ዘገባዎች መካከል የእንግሊዙ ንጉሥ ጆርጅ እረፍትና እሳቸውን ተከተው ወደ ንግስናው የመጡት ንግስት ኤልሳቤጥ ጉዳይ አንዱ ነው። በቅርቡ ያረፉት ንግሥት ኤልሳቤጥ በወቅቱ ወደ ንግስና ሲመጡ በጋዜጣው የፊት ሙሉ ገፅ ሽፋን አግኝቶ ነበር። ከጋዜጣው ዘገባ መካከል የንጉሡን ዕረፍት የተመለከተውን የመጀመሪያ ዜና ለዛሬ መርጠን የምናስታውሳችሁ ሲሆን፣ የውጭ አገር ሰዎች በጅማ ቡና ገበያና በጫካው ቡና መደነቃቸውን በዚህም የንግድ ቤት ለመክፈት እንደወሰኑ የሚነገረንን ዘገባም መርጠናል። በተጨማሪም በያኔው ዘመን ምርትና ወንጀል ነክ እንዲሁም አደጋ ተኮር ዘገባዎችንም እንደሚከተለው አካተን ቀርበናል።**

**ስለ ግርማዊ የእንግሊዝ ንጉሥ ጆርጅ ዕረፍት**

**ጥር ፳፰ ቀን ከሬውተር**

**ሎንዶን**

ግርማዊ ንጉሥ ጆርጅ ዛሬ ጥር ፳፰ ቀን ፲፱፻፵፬ ዓ.ም ጠዋት በመኝታቸው ላይ ሳሉ በማረፋቸው የበከር ልጃቸው ልዕልት ኤልሳቤጥ ወዲያውኑ የእንግሊዝ ንግሥት ሆነዋል።

የንጉሥ ጆርጅ ዕድሜያቸው ፶፮ ዓመት ነው። ታላቅ ወንድማቸው ኤድዋድ ስምንተኛ በ፲፱፻፳፱ ዓ.ም አልጋውን በለቀቁ ጊዜ ግርማዊ ንጉሥ ጆርጅ ፮ኛ በእንግሊዝ መንግሥት ዙፋን ላይ ተቀመጡ።

ዕድሜያቸውን ሙሉ እንደ አንድ ተራ ሰው ለመሆን ይሞክሩ በነበሩት ንጉሥ ዕረፍት የእንግሊዝ ሕዝብ ጥልቅ ሀዘን ተሰምቶታል። ሕዝቡ ንጉሡ ብዙ ጊዜ ታመው ከባድ የሆነ ኤፕራሲዮን ከተደረገላቸው በኋላ ጤናቸው ይመለስላቸዋል በማለት ተስፋ ያደርግ ነበር።

ጠቅላይ ሚኒስትሩ ሚስተር ቸርችል የንጉሡን ዕረፍት እንደ ሰሙ ወዲያውኑ ምክር ቤቱ እንዲሰበሰብ አድርገው ፤ ምክር ቤቱ ስለ ሕዝቡ ሐዘን ጠቅላይ ሚኒስትሩ የሚያደርጉት መግለጫ ለመስማት ከሰዓት በኋላ ስብሰባ አድርጎ ነበረ።

ልዕልት ኤልሳቤጥ የኮመንዌልዝ አገሮችን ለመጎብኘት ከባለቤታቸው ከፕሪንስ ፊሊፕ (የኤዲንበራካዱ) ጋር በመንገዳቸው ላይ ሳሉ ለጊዜው በሚገኙበት ኬንያ ውስጥ ናሪያ በምትባል ስፍራ የንጉሡ መሞት ወሬ ደረሳቸው። ዕድሜያቸው ፳፭ ዓመት የሆናቸው ልዕልት ከአምሳ ዓመት ወዲህ ለመጀመሪያ ጊዜ ንግሥት ሆኑ። ንግሥት ቪክቶሪያ ያረፉት በ፲፰፻፺፫ ዓ.ም ነው።

**(የካቲት ፩ ቀን ፲፱፻፵፬ ዓ.ም ከወጣው አዲስ ዘመን )**

**የእሳት አደጋ ጠባቂዎች ትጋት**

መስከረም ፩ ከጠዋቱ ፫ ሰዓት ተኩል ሲሆን በአቡነ ጴጥሮስ መንገድ በቤንዚን ማደያው አጠገብ ከፍ ያለ የእሳት አደጋ ተነስቶ የ፩ኛና የ፪ኛ እሳት አደጋ ተጠባባቂዎች በፍጥነት ደርሰው በኃይል ተከላክለው ቃጠሎውን አጥፍተውታል። አደጋው የተነሳው ከቤንዚን ማደያው አቅራቢያ ከሰል ነጋዴዎች በመኖራቸውና እሳትም ከዚያ ውስጥ በማንደዳቸው ሲሆን፤ እንዲሁም ቤንዚን ቀጂዎች በቁርቁሮ እየቀዱ ከዚያው ቤት በማስቀመጣቸው ነው።

ቤንዚን ይዞ ወደ ከሰሉ እሳት ቀርቦ ለቃጠሎው መነሻ የሆነው ሰው በጣም ቆስሎ ከራስ ደስታ ሆስፒታል ሲገባ የእሱው አባሪ የሆኑ ሦስት ልጆች ጥቂት ቆስለው ነበርና የእሳት አደጋ ተጠባባቂዎች በመድኃኒት ወዲያውኑ አክመዋቸዋል። ቁስሉም ለጉዳት አይሰጣቸውም።

የእሳት አደጋ ተጠባባቂዎች በፍጥነት ባይደርሱ ኖሮ ይህ አደጋ በቤንዚን ማደያ አጠገብ በመሆኑ አስጊ ሳይሆን አይቀርም ነበር። ይልቁንም በማዘጋጃ ቤት አማካይነት አሁን በቅርብ ጊዜ የመጡት የእሳት አደጋ መጠባበቂያ መኪናዎች በዚሁ አደጋ ላይ አገልግሎታቸውን በማሳየታቸው በሕዝቡ ዘንድ ተመስግነዋል።

ስለዚህ ይህን የመሰለ ከፍ ያለ አደጋ በከተማው እንዳይደርስ ከሰል ነጋዴዎች ከቤንዚን ማደያ አቅራቢያ እንዳይገኙ ማድረግ የሚገባ ነው።

**(መስከረም 18 ቀን 1944 ዓ.ም ከወጣው አዲስ ዘመን )**

**በጥፋታቸው ስለተቀጡ ወንጀለኞች፤**

**ከወንጀል ምርመራ ክፍል**

**የተገኘ ሁኔታ**

፩ኛ ጥላሁን ከበደ፤ ፪ኛ ቶሎሣ ገብረማርያም፤ ፫ኛ ተክሌ ወልደማርያም፤ ፬ኛ ዘውዴ ንጉሤ፤ ፭ኛ ገበየሁ ካሣ፤ ፮ኛ መንግሥቱ ደስታ፤ ፯ኛ ከበደ ኃይሉ፤ ፰ኛ ደስታ በላይ፤ ፱ኛ አረሩ ገብረ ወልድ ከ፩ኛ እስከ ፱ኛ ተራ ቁጥር የተከሰሱት ወንጀለኞች ከነሐሴ ወር ፴፪ ዓ.ም ጀምረው በየጊዜው በከተማው ውስጥ እየተዘዋወሩ ቤት እየሰበሩና ግድግዳ እየማሱ በመስረቅ ከቆዩ በኋላ ነሐሴ ፳፪ ቀን ፴፫ ዓ.ም በወንጀለኛ ምርመራ ፖሊሶች ትጋት ተይዘው በምርመራ የሰረቁባቸውን ሰባ አራት ቤቶች መርተው ተቀባዮቻቸውን አስያዙ።

ከዚህ በኋላ ጥቅምት ፲፰ ቀን ፴፬ ዓ.ም ከፍተኛው ፍርድ ቤት ቀርበው የእምነትና የክህደት ቃላቸውን ተጠይቀው ጉዳዩ እንደገና ለጥቅምት ፳ ቀን ፴፬ ዓ.ም ተቀጠረ።

በዚህ ቀን በ፯ኛው ቁጥር የተጠቀሰው ብቻ ታሞ ሲቀር ፰ቱ ወንጀለኞች እያንዳንዳቸው ፪ ሁለት ዓመት እሥራትና አርባ ፵ ጅራፍ ግርፋት ተፈርዶባቸዋል። የነዚሁ ወንጀለኞች ተቀባይ ሆነው የተገኙ ሰላሣ አንድ ሰዎች በተለይ ፋይል ተከፍቶ በፍርድ ላይ ናቸው።

**(ኅዳር 14 ቀን 1944 ከወጣው አዲስ ዘመን )**

**የቡና አዝመራ**

በከፋ ጠቅላይ ግዛት ቡና የሚለቀምበትና የሚሸጥበት ወራት አሁን በመሆኑ በያሉበት ገበያዎች ተሟሙቀው ካሚዮኖቹም ሲመላለሱ ይታያሉ። በተለይ ጅማና አጋሮ ሐሙስና ማክሰኞ ከየአገሩ ገበያተኞችና ነጋዴዎች የሚጎርፉበት ቀን ስለሆነ በዚህ ገበያ ቀን በመኪናና በሰው ብዛት የተነሣ መተላለፊያ አይገኝም።

ብዙ የውጭ አገር ሰዎች የዕረፍታቸውን ጊዜ ለማሳለፍ ጅማ ከተማ በትልቁ ሆቴል አርፈው በአገሩ ውስጥ እየተዘዋወሩ በቡናው ጫካና በአገሪቱም ሀብታምነት፤ በእርሻውና በየኮረብታዎቹ ውበት መደሰታቸውን ገልጸዋል።

ብዙ ነጋዴዎች ከአዲስ አበባ፤ ከሌላውም አገር ቤት እየመጡ የንግድ ቤት ለመክፈት ፈቃድ ጠይቀዋል። በአዲስ አበባ የሚገኙ ትልልቅ ንግድ ቤቶች ቅርንጫፋቸውን ለማቋቋም ሰዎችን ልከዋል። በዚህ አኳኋን የጅማ ከተማና ንግዱ እየተስፋፋ የሚሔድ መስሎ ይታያል።

**የጅማ ተሳሳኪያችን ።**

**(ጥር 17 1944 ዓ.ም ከወጣው አዲስ ዘመን)**

# ዓለም አቀፍ

## የአልሸባብ መሪ አብዱላህ ናዲር በድሮን ጥቃት ተገደለ

ዋቅሹም ፍቃዱ

**አዲስ አበባ፡-** አብዱላህ ናዲር የተባለው የአልሸባብ ቡድን መስራችና ከፍተኛ መሪ በሶማሊያ በድሮን ጥቃት መገደሉን ቢቢሲ አስነብቧል።

ቢቢሲ የሶማሊያ የቱሪዝም፣ ባህልና ማስታወቂያ ሚንስቴርን ጠቅሶ እንደ ዘገበው፣ የአሸባሪው አልሸባብ ታጣቂ መሪ የነበረው ይህ ግለሰብ በሶማሊያ የጸጥታ አካላት ለረጅም ጊዜ ክትትል ሲደረግበትና በጥብቅ ሲፈለግ ነበር። ግለሰቡ የተገደለው ባለፈው ቅዳሜ በሶማሊያ ደቡባዊ የጁባ ግዛት በተወሰደ የተቀናጀ ኦፕሬሽን መሆኑን የሶማሊያ ባለሥልጣናት ሲገልጹ፣ የግል ሚዲያዎች ግን ግለሰቡ ሊገደል የቻለው በድሮን ጥቃት መሆኑን አስነብቧል።

አብዱላህ ናዲር የሃይማኖት ማስፋፊያ ዘር ኃላፊ በመሆን ለዘመናት የተለያዩ የሽብር ተግባር ሲፈጽምና ሲያስፈጽም የነበረ መሪ ሲሆን ቀደም ሲል አሜሪካ ግለሰቡ ያለበትን ቦታ ለሚጠቁም ወይም አሰልፎ ለሚሰጥ አካል 3 ሚሊዮን ዶላር ጉርሻ ይፋ ማድረጓን ቢቢር ጠቅሷል።

በተመሳሳይ መልኩ አብዱላህ ናዲር በአሁኑ ጊዜ ከፍተኛ የጤና እክል እንደገጠመው በስፋት የሚነገረው የአልሸባቡ መሪ አሕመድ ኦማር አከ አቡ ኡባይደሃ ይተካል ተብሎ ተስፋ ተጥሎበት እንደነበር ቢቢሲ የማስታወቂያ ሚንስቴሩን ጠቅሶ ገልጿል።

ብዙውን ጊዜ በአልሸባብ መሪዎች ላይ የተቀናጀ ጥቃት የሚወስዶ የአሜሪካ-አፍሪካ ኮማንድ ዩንት በአዱላህ ናድር ግድያ ላይ ያለው ነገር ባይኖርም በቡድኑ ላይ እየተወሰደ ባለው የተቀናጀ እርምጃ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ የሶማሊያ ሚሊሾች እንኳ በቡድኑ ላይ ድል እየተቀዳጁ ይገኛሉ። ቡድኑ ከጊዜ ወደ ጊዜ ኪሳራ እየደረሰበት ቢሆንም የተስፋ መቁረጥ ጥቃቶች እየፈጸመ ይገኛል።

የመሪውን መገደል ተከትሎ በድኑ ሰኞ ዕለት በሶማሊያ በበለድዩዋ ከተማ ሁለት የቦምብ ጥቃቶች መፈጸሙንና ለጊዜው ያደረሰው ጉዳት ይፋ እንዳልሆነም ቢቢሲ የአገሪቱን ብሔራዊ ቴሌቭዥን ዘገባ ጠቅሶ አስነብቧል።

ጠንካራ የሶማሊያ መንግሥት በመባል የሚታወቀው የመሀመድ ሲያድ ባሬ መንግስት እ.ኤ.አ 1991 ከተገረሰሰ ወዲህ የተፈጠሩት አለመግባባቶች አገሪቱ እንዳትረጋጋ ከማድረግ ባሻገር ለጽንፈኛው የአልሸባብ ቡድን መፈጠር ምቹ ሁኔታን መፈጠሩን ከብሪታኒካ ኮሚ ድረ -ገጽ የተገኘው መረጃ ያመላክታል።

ቡድኑ እ.ኤ.አ 2004 በደቡባዊ ሶማሊያ የተመሰረተ ሲሆን በእስላማዊ ፍርድ ቤቶች ኅብረት የጠበቀ የጋራ ግንኙነት ያለው ሚሊሻ ሲሆን በአገሪቱ ለተስተዋለው ሥርዓት አልበኝነትና ዝርፊያ ግንባር ቀደም ተዋናይ ነው። ከ2006 ጀምሮ ግን ከአልቃይዳ ጋር ግንኙነት ያለው የሶማሊያን የኢስላማዊ ታጣቂ ቡድን መሆኑን በግልጽ ካወጀ በኋላ የሶማሊያ ሽግግር መንግስት እንዳይሳካና እንዳይረጋጋ ከፍተኛ ጫና ሲያደረግ ቆይቷል።

አልሸባብ በሶማሊያ ከሚወስዳቸው የሽብር ተግባር በተጨማሪ በተለያዩ ጊዜያት በአፍሪካና በተባበሩት መንግስታት የሰላም አስከባሪዎች የተለያዩ ሙከራዎችን ማድረጉን የብሪታኒካ ኮሚ ድህረ ገጽ ያትታል። ድንበር አልፎ በጎረቤት አገራት በወሰዳቸው የሽብር ጥቃቶች የዓለም ጠላት መሆኑን አስመስክሯል።

ኡጋንዳ አልሸባብን ለመዋጋት ወታደሮቿን ለአፍሪካ የሰላም አስከባር ሀይል/ለአሚሶም በማወጣቷ ምክንያት ብቻ ቡድኑ ድንበር ዘልሎ እ.ኤ.አ 2010 በኡጋንዳ በአንድ ላይ ሆነው የዓለም እግር ኳስ ዋንጫ በሚከታተሉ ወጣቶች ላይ በወረወረው ቦምብ በጥቂቱ የ75 ሰዎች ሕይወት መቅጠፍ ችሏል።

እ.ኤ.አ 2013 በኬንያ ኢስት ጌት በሚባለው ትልቁ የገበያ አዳራሽ ላይ በወሰደው ጥቃት 65 ሰዎች ሕይወታቸውን ሲያጡ፣ በተመሳሳይ መልኩ ቡድኑ ከሁለት ዓመት በኋላ በ2015 በሀገረ ኬንያ ገሪሳ ዩኒቨርሲቲ ላይ በወሰደው እርምጃ የ140 ሰዎች ሕይወት ቀጥፏል። በቅርብ ጊዜ የኢትዮጵያን ድንበር ጥሶ በመግባት ያቀደው ተመሳሳይ የጥፋት ድርጊቱ መክሸፉ ይታወሳል።



የመፈንቅለ መንግስቱ ደባብ

## የምዕራብ አፍሪካ አገራት ሸምጋዮች ወደ ቡርኪናፋሶ አቅንተዋል

ዋቅሹም ፍቃዱ

አዲስ አበባ፡- የሰሞኑ መፈንቅለ መንግስት ጋር ተያይዞ ሌተናል ኮሎኔል ፖል ሄንሪ ሳንዳጎ ከአገር መውጣት ተከትሎ በአገሪቱ መረጋጋት እንዲሰፍን የምዕራብ አፍሪካ አገራት ሸምጋዮች ወደ ቡርኪናፋሶ ማቅናታቸውን አሶሼትድ ፕሬስ ዘግቧል፡፡

መፈንቅለ መንግስት ለማስተናገድ የተገደደችው የምዕራብ አፍሪካዊቷ አገር አሁናዊ ሁኔታ ውጥረት አስፈሪ ሆኗል፡፡ የተፈጠረው አለመረጋጋት ስር ሰድዶ በአገሪቱ የሚንቀሳቀስ ጽንፈኛው የኢስላማዊ ቡድን ሰፊ እድል እንዳያገኙና እ.ኤ.አ በ2024 ወርሃ ሐምሌ ለማካሄድ ታቀደው የአገሪቱ ምርጫ እንዳይራዘም የምዕራብ አፍሪካ መንግስታት የኢኮኖሚ ማህበረሰብ /ኢኮዋስ/ ከፍተኛ ርብርብ ላይ ይገኛል፡፡

የአገሪቱ የሃይማኖት መሪዎች ሸምጋይነት ሌተናል ኮሎኔል ፖል ሄንሪ ሳንዳጎ ዳሚባ አገሪቱን ለቀው ወደ ጎሮቤት አገር ቶጎ ከተሰደዱ በኋላ አዲሱ የቡርኪናፋሶ መሪ ካፒቴን ኢብራሂም ትራኦሬ ምርጫውን በመጠባበቅ ላይ ያሉ የመንግስት መሪ መሆናቸውን የጁንታ እሑድ እለት ሲያስታውቅ ኢኮዋስ ግን በተቃራኒው አገሪቱን የሚመራ መሪ በምርጫ የሕዝብ እውንታ ያገኘ ብቻ እንደሚሆን ማስታወቁን አሶሼትድ ፕሬስ በዘገባው አመላክቷል፡፡

ካፒቴን ኢብራሂም ትራኦሬ የአገሪቱን ነባራዊ ሁኔታ አስመልክተው ለአሜሪካ ድምጽ በሰጡት አስተያየት፣ በአገሪቱ ቀደም ሲል ጽንፈኛው የኢስላማዊ ቡድን በአገሪቱ በአቀጣጠሉት አመጽ ብዙዎቹ ሲሞቱ 2 ሚሊዮን የሚሆን ሕዝብ ከቤት ንብረቱ ተፈናቅለዋል፡፡

በአገሪቱ አንዳንድ አካባቢዎች የከፋ ረሃብ ከመከሰቱ የተነሳ ሰዎች ሕይወታቸውን ለማዳን ሲሉ ያገኙትን የዛፍ ቅጠልና የተለያዩ አረሞች ለመመገብ ተገደዋል ያሉት ካፒቴን ኢብራሂም፣ ሕዝቡን ለመታደግ የተለያዩ የመፍትሔ አማራጮች ቢያቀርቡም የሚሰማቸው ሰው እንደሌለ ይገልጻሉ፡፡

አንዳንድ የአገሪቱ ዜጎች ጽንፈኛው የኢስላማዊ ቡድን ለመዋጋት በማሊ እንደተደረገ ሁሉ የራሺያ ወታደራዊ ድጋፍ እንደሚሹ ሲሆን በአንጻሩ ደግሞ የራሺያ ወታደሮች ለድጋፍ ወደ አገሪቱ ከገቡ በሚፈጽሙት ሰብዓዊ ቀውስ ያለው ሁኔታው ተባብሶ ከቁጥጥር ውጭ እንደሆን የሚቃወሙ ዜጎች መኖራቸውን በዘገባው ተገልጿል፡፡

በአንጻሩ ለመፈንቅለ መንግስቱ መሪ ከለላ በመስጠት የምትወነጀለው ፈረንሳይ የቡርኪናፋሶ የተፈጠረው ቀውስ አደገኛ መሆኑን ገልጻ፣ በአገሪቱ የሚኖሩ 4 ሺህ ዜጎቿ ከቤት እንዳይወጡ ማስጠንቀቋን የአሶሼትድ ፕሬስ ዘገባ አመላክቷል፡፡

The Ethiopian Herald
አዲስ ዘመን
BARIISAA
العلم
ወጋሕታ
BAKKALCHO
ዘመን
የህትመት ውጤቶቻችንን ለማንበብ ድረገጻችንንና ፌስቡክ ገጻችንን ይጎብኙ!
የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት
ዌብሳይት፡- www.press.et
ፌስቡክ፡- Ehiopian Press Agency

አዲስ ዘመን
ማክሰኞ ስፖርት

ይህ ቦታ ለማስታወቂያ ክፍት ነው!

# ኢትዮጵያዊያን አትሌቶች በጎዳና ላይ ውድድሮች የደመቁበት ሳምንት

**ብርሃን ፈይሳ**

እየተገባደደ በሚገኘው የመስከረም ወር በተለያዩ የዓለማችን ታላላቅ ከተሞች በርካታ የጎዳና ላይ የሩጫ ውድድሮች መካሄዳቸው የተለመደ ነው:: ባለፈው ሳምንት መጨረሻም በተመሳሳይ ከ5ኪሎ ሜትር አንስቶች እስከ ማራቶን በቁጥር በዛ ያሉ ውድድሮች ተካሂደዋል:: በእነዚህ ውድድሮች ላይም ኢትዮጵያን ጨምሮ የምስራቅ አፍሪካ አትሌቶች ውጤታማ ለመሆን ችለዋል::

ኢትዮጵያዊያን አትሌቶች በሁለቱም ጾታ ድል ካደረጉባቸው ውድድሮች መካከል አንዱ በጣሊያን የተካሄደው የትሬንቶ ግማሽ ማራቶን ውድድር ነው:: የግራዳ ሃይቅን ተንተርሳ በተቆረቆረችው ትሬንቶ ከተማ ለጎብኚዎች ተመራጭና ከየዓለምቱ የሚመጡ ቱሪስቶች መዳረሻ መሆኗ ይነገርላታል:: በዚህች ታሪካዊ ከተማም የሃይቁን ዳርቻ ተከትሎ የሚካሄድ ዓመታዊ የጎዳና ላይ የሩጫ ፌስቲቫል ይታወቃል:: እአአ 1907 ጀምሮ የሚካሄደው ይህ ፌስቲቫል ታዋቂ አትሌቶችን ጭምር በማሳተፍ የሚካሄድ ሲሆን፤ ከዚህ ቀደም ቀነኒሳ በቀለን፣ ፓውል ቴርጋትንና ስቴፋኖ ባልዲኒን የመሳሰሉ ከዋክብት ሮጠውባታል::

ባለፈው ሳምንት መጨረሻ በተካሄደው የዘንድሮው የሩጫ ፌስቲቫል ላይም ኢትዮጵያዊያንና ኬንያዊያን አትሌቶችን ጨምሮ በርካታ ታዋቂ አትሌቶች ተካፍለውበታል:: በወንዶች በኩል በተካሄደው ውድድርም የማራቶን የዓለም ቻምፒዮኑ አትሌት ታምራት ቶላ ስኬታማ መሆን ችሏል:: እአአ በ2017ቱ የለንደን ዓለም ቻምፒዮና የነሃስ ሜዳሊያ ባለቤት የነበረው ታምራት ከወራት በፊት በአሜሪካዋ ኦሪጎን በተካሄደው የዓለም ቻምፒዮና የወርቅ ሜዳሊያውን በማጥለቅ አገሩን ማስጠራቱ የሚታወስ ነው:: አትሌቱ በተካፈለበት በዚህ የግማሽ ማራቶን ውድድር ላይም የተለመደ ብቃቱን በማስመስከር አሸናፊ ሆኖ ለመፈጸም በቅቷል:: ታምራት ርቀቱን ለማጠናቀቅ የፈጀበት ሰዓትም 59:49 ሲሆን፤ ይህም የቦታው ፈጣኑ ሰዓት ሆኖ ተመዝግቦለታል::



አትሌት ታምራት ቶላ የትሬንቶ ግማሽ ማራቶን ውድድርን አሸናፊ ሆኗል፣

በዚሁ የሩጫ ፌስቲቫል ላይ ከሚካሄዱ ውድድሮች መካከል አንዱ የ10ኪሎ ሜትር ሲሆን፤ በዚህም ኢትዮጵያዊው አትሌት ሙክታር ኢድሪስ ቀዳሚ መሆን ችሏል:: የሁለት ጊዜ የመም ረጅም ርቀቶች የዓለም ቻምፒዮና መሆን የቻለው አትሌቱ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በጎዳና ላይ ሩጫዎች ላይም እየታየ ይገኛል:: በጣሊያን በተካሄደው በዚህ ሩጫ ላይም ርቀቱን 28:47 በሆነ ሰዓት በመሮጥ፤ ከተፎካካሪዎቹ ጋር ሰፊ ልዩነት በማሳየት ባለድል ለመሆን ችሏል::

ኬንያዊው አትሌት ዌስሌይ ኪሙታይ ታምራትን ተከትሎ በመግባት ሁለተኛ ደረጃን መያዝ ችሏል:: ጠንካራ ተፎካካሪ የነበረው ይህ አትሌት እጅግ ተቀራራቢ በሆነ ሰዓት 1:00:45 በማስመዝገብ ነው ውድድሩን ያጠናቀቀው:: ዩጋንዳዊው አትሌት ኬቨን ኪቤት ሶስተኛ ሲሆን፤ ኢትዮጵያዊው ሌሊሳ አራርሳ ደግሞ አራተኛ ደረጃን ይዟል::

በሴቶችም በተመሳሳይ የውድድሩ አሸናፊ የሆነችው አትሌት ኢትዮጵያዊት ናት:: በተለይ በማራቶን ውድድሮች የምትታወቀው አትሌት ብሩክታይት ደገፋ የውድድሩ አሸናፊ ሆናለች:: አትሌቷ ርቀቱን የሮጠችውም 1:09:41 በሆነ ሰዓት ነው:: በጥቂት ሰከንዶች ልዩነት ሁለተኛ የሆነችው ኬንያዊቷ አትሌት ኢማኳሌት ቼፕኪሩይ 1:09:47የሆነ ሰዓት አስመዝግባለች:: ሌላኛዋ ኢትዮጵያዊት አትሌት ደሴ አንቺንአሉ ደግሞ 1:09:58 በሆነ ሰዓት ሶስተኛ ሆና ገብታለች::

በዓለም ዙሪያ ከሚካሄዱ ዓመታዊ የግማሽ ማራቶን ሩጫዎች መካከል ታዋቂ ከሆኑት መካከል በሚመደበው የካርዲፍ ግማሽ ማራቶንም ኢትዮጵያዊያን አትሌቶች ተካፋይ ነበሩ:: በዌልስ ዋና ከተማ ካርዲፍ የሚካሄደው ይህ ውድድር እአአ በ2003 የተጀመረ ሲሆን፤ ኬንያዊያን አትሌቶች የተሻለ የስኬት ታሪክ አላቸው:: በዘንድሮው ውድድር ላይም በተመሳሳይ ኬንያዊው ጂኦፍሪ ኮች 1:00:01 የሆነ ሰዓት በማስመዝገብ አሸናፊ ለመሆን ችሏል::

ኢትዮጵያዊያኑ አትሌቶች ለኬንያዊው ብርቱ ፈተና ቢሆኑበትም በሰከንዶች ዘግይተው አሸናፊነቱ ቦታ ሊወሰድባቸው ችሏል:: በዚህም ጊዜአለው አበጀ 1:00:17 የሆነ ሰዓት በማስመዝገብ ሁለተኛ ደረጃን ሲይዝ፤ ጪምዴሳ ደበሌ ደግሞ በአገሩ ልጅ በአንድ ሰከንድ ብቻ ተበልጦ ሶስተኛው አትሌት ሆኗል:: በሴቶች በኩል አንደኛ እና ሁለተኛ የሆኑት ኬንያዊያን አትሌቶች ሲሆኑ፤ ኢትዮጵያዊያኑ አትሌቶች ዘውዲቱ አደራው እና ብርሃን ምህረቱ ሶስተኛ እና አምስተኛ ደረጃን ይዘው ሊያጠናቅቁ ችለዋል::

የኢትዮጵያ ኅብረት ሥራ ኮሚሽን
Ethiopian Cooperative Commission
(ECC)
ከኢትዮጵያ ኅብረት ሥራ ኮሚሽን ጋር በመተባበር
በየሳምንቱ የሚታተም

# እሴት የተጨመረባቸውን የወተት ምርቶች ለገበያ እያቀረበ በዕድገት ጎዳና ላይ ያለ ኅብረት ስራ ዩኒየን

**በዳኛቸው ቀደማቸው**

ጎጃም ወተት ልማትና ግብይት ህብረት ስራ ዩኒየን በአማራ ክልል ምስራቅ ጎጃም ዞን ደጀን ወረዳ በየትኖራ ከተማ ላይ ይገኛል። ዩኒየኑ በዞኑ የወተት ልማት ግብይት ልማት እንዲስፋፋ አደረጃጀቱን እና አሰራሩን እለት በእለት እያጠናከረ በመስራት ላይ ይገኛል:: ኅብረት ስራ ማህበራት በስፋት ከአባሎቻቸው ግብይቶችን በብቃት በማቅረብ ቀጣይነትና ተከታታይነት ባለው ሁኔታ ምርቶችን የሚረከቡ ቢሆኑም፤ በአብዛኛው ገበያው ከወቅታዊ ፍላጎት ላይ በተለይም በፆም ወቅት በሚፈጠር የወተት ፍላጎት መቀነስ ጋር ተያይዞ በአብዛኛው የምርት ብልሽትና ብክነት የሚፈጠርበት ሁኔታ በመኖሩ አባላት በተደጋጋሚ ኪሳራ ውስጥ ሲገቡ ቆይተዋል::

በመሆኑም እነዚህን መሰረታዊ የወተት ልማትና ግብይት ኅብረት ስራ ማህበራት ዩኒየን ማቋቋም አስፈላጊ በመሆኑ የጎጃም ወተትና ግብይት ልማት ኅብረት ስራ ዩኒየን ታኅሳስ 2007 ዓ.ም በአራት መስራች መሰረታዊ ማህበራት፣ በሁለት ወረዳዎች፣ በ534 ሺ ብር ካፒታል የተመሰረተ ነው:: በአሁኑ ሰዓት በሰባት ወረዳዎች የአባል መሰረታዊ ማህበራትን ቁጥር 12 የአርሶ አደር አባላትን ደግሞ አንድ ሺ 442 በማድረስ የካፒታል መጠኑን ብር ከዘጠኝ ነጥብ አምስት ሚሊዩን ብር በላይ በማድረስ የወተት ምርትን መጠን እንዲጨምር ብሎም ወተትን በማቀነባበር እሴት ጨምሮ ለተጠቃሚው በማድረስ ላይ ይገኛል::

በቀጣይም የአባላትን ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ዕድገት ለማምጣት የሚያስችል ዓላማን በማንገብ ከእያንዳንዱ አርሶ አደር ጀምሮ በየደረጃው በመዋቅራዊና ኢኮኖሚያዊ ቅንጅት በመፍጠር በራስ መተማመን በማጎልበት የአባል ማህበራትን ብሎም የሰፊውን ህብረተሰብ ጥቅም የማረጋገጥ ተልዕኮ ሰንቆ እየሠራ ይገኛል:: ጎጃም ወተት ልማትና ግብይት ህብረት ስራ ዩኒየን በስድስት ሚሊየን ብር የወተት ማቀነባበሪያ ፋብሪካ ገንብቶ ፓስቸራይዝድ ወተት፣ ፓስቸራይዝድ እርጎ ፣ የምግብ ቅቤ ፣ የጸጉር ቅቤና አይብ ለአካባቢው ማህበረሰብ እያቀረበ ይገኛል:: ዩኒየኑ በአንድ ወቅት በካፒታል እጥረት ምክንያት ችግር አጋጥሞት መንግስታዊ ባልሆነ ተቋም (አግሪቴራ) ድጋፍ መልሶ ወደ ማምረት ስራ ገብቷል። ከፍተኛ ጥራት ያላቸውን፣ ትኩስ ምርቶችን በቀጥታ ከገበሬዎች፣ እንዲሁም ተፈጥሯዊ ጣዕማቸውን የጠበቁትንና ጥራት ያላቸውን ምርቶችን ለቀመሰው ሰው በተለይ የእርጎው ክሬም ስሜትን ያማልላል። ጎጃም ወተት ግብይት ኅብረት ስራ ማህበራት ዩኒዩን አባላት "ወተት እንደ ጅረት" ቢያመርቱም ብራንድ በሆነው ምርታቸው እሴት ተጨምሮበት በስፋት ወደ ገበያ ባለመግባቱ በሚፈለገው ደረጃ ተጠቃሚ እየሆኑ አይደለም:: ጎጃም ናፈቀኝ፣ ጎጃም ናፈቀኝ፣ ማርና ወተቱ ናፈቀኝ እሸቱ................ ተብሎ የተዘፈነለት ጎጃም....... እውነትም በተግባር የማርና የወተት አገር መሆኑ ጎጃም ወተት ግብይት ኅብረት ስራ ማህበራት ዩኒዩን ያለው ኦርጋኒክ እርጎና ቅቤ ምርት ህያው ምስክር ነው ማለት ይቻላል::



በዩኒየኑ ጥሬ ወተት የሚሰበሰበው በስሩ ከሚገኙ 12 አባል መሰረታዊ ኅብረት ስራ ማህበራት በእነዚህ መሰረታዊ ማኅበራት ስር አንድ ሺ 461 አርሶ አደሮች ሲሆን በቀን 10 ሺህ ሊትር ወተት በማሰባሰብ እሴት በመጨመር ለገበያ ማቅረብ ቢኖርበትም በአሁኑ ሰዓት በቀን የሚያመርተው አምስት መቶ ሊትር ወተት ብቻ ነው:: ለዚህም ዋናው ምክንያት የካፒታል፣ የትራንስፖርትና የፋብሪካ ብልሽት ችግር መሆኑን ሰራተኞቹ አስረድተውናል:: ከዚሁ ጋር ተያይዞ እሴት በመጨመር የተለያዩ ምርቶችን በማምረት በምስራቅ ጎጃም ዞን የተሰጠውን የወተት ብራንድ በማጉላት በአገሪቷ ተወዳዳሪ በመሆን ምርቱን ወደ ሌሎች ከተሞች ተደራሽ ማድረግ አልተቻለም በማለት የዩኒዩኑ ስራ አስኪያጅ የሆኑት አቶ አቤል ታምራት ገለፀዋል::

ይህ በእንዲህ እንዳለ ዩኒዩኑ ጥሬ ወተት በመቀበል እሴት ጨምሮ በመሸጥ አምራች ማህበረሰቡንም ሆነ የማህበሩን አባል በሚፈለገው ደረጃ ተጠቃሚ እያደረገ አይደለም:: አቶ ሰይፉ መከተ የዚባ ወተት ግብይት ኅብረት ስራ ማህበር አባል ናቸው:: ከመንግስት ስራቸው ጎን ለጎን የወተት ላሞችን በማርባትም በከተማ ግብርና እየሰሩ መሆኑን ተናግረዋል:: ካሏቸው ስድስት ላሞች እስከ ሃያ አምስት ሊትር ወተት በየቀኑ በማቅረብ በወሩ መጨረሻ እስከ 25 ሺህ ብር ገቢ እያገኙ ነው:: ይህም ትልቅ ኢኮኖሚያዊ ለውጥ እንደሚያመጣልን እናምናለን" ብለዋል::

ሌላው የማኅበሩ አባል አቶ አማረ ጌታቸው ወደ ማኅበሩ ከተቀላቀሉ አንድ ዓመት እንደሆናቸው ገልጸው፤ ወተት በማቅረብ በየወሩ እስከ ሶስት ሺህ አምስት መቶ ብር ድረስ እያገኙ ነው:: በተጨማሪም በወተትና ወተት ተዋጽኦ ሕብረት ሥራ ዩኒየን ተደራጅተው በመስራታቸው በነፍስ ወከፍ የሚያገኙት ገቢ እስከ 21 ሺ 600 ብር በማግኘት ተጠቃሚ መሆናቸውን ለማህበራቸው ከጠዋቱ 12 ሰዓት ላይ ወተት ሲያስረክቡ ያገኘናቸው እናት አርሶ አደር ወይዘሮ አዳነች አድገህ ገልጸዋል። አርሶ አደሯ አክለውም በዩኒዩን መደራጀታቸው በገበያ እጦት ምርታቸው እንዳይባክን እንደረዳቸውም ጨምረው ተናግረዋል።

የወተት ግብይቱን ለማዘመንና ተደራሽ ለማድረግ በፋብሪካው እሴት በመጨመር ለህብረተሰቡ ንፁህ ምርት በማቅረብ ብራንድ የሆነውን ተፈጥሯዊ ጣዕሙን የጠበቀውን ወተት ደረጃውን አስጠብቆ በስፋት ለገበያ ማቅረብ እየሰራን ነው ሲሉ የምስራቅ ጎጃም ዞን ኅብረት ስራ ማስፋፊያ ተጠሪ ፅህፈት ቤት ሃላፊ አቶ ሙሉቀን ቢያድግልኝ ተናግረዋል::

የጎጃም ወተት ልማትና ግብይት ህብረት ስራ ዩኒየን አሁን በጀመረው የስኬት ጎዞ እንዲሄድ በአደረጃጀት፣ በአሰራርና በሰው ኃይል የጀመረውን ማኅበሩን የማጠናከርና የማዘመን ስራ አጠንክሮ መቀጠል ይገባዋል:: በተለይ ከህዝብ ጤንነት ጋር በተያያዘ ወተት በቀላሉ የመበላሻት እና የመመረዝ ባህሪ ስላለው፣ የወተት ምርቱን በጥንቃቄ በቴክኖሎጂ ተደግፎ የመያዝ አስፈላጊነትን ለነገ የሚባል ጉዳይ ስላልሆነ፣ ዩኒየኑ አሁን የጀመረውን ወተትን በጥራት የመያዝ ስራ አጠናክሮ እንዲቀጥል አደራ ልንል ይገባል::

አድራሻ | የፌዴራል ኅብረት ሥራ ኮሚሽን | 0115573448/ 0118592105 | ፖ.ሳ.ቁ. 19787 | Facebook: Federal cooperative Agency | Website: www.fca.gov.et